# የአዲስ አበባ ከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ

## የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር

56/2013

የመጀመሪያ እትም

አዲስ አበባ ጤና ቢሮ

ግንቦት 2001

# ምዕራፍ አንድ፡ አጠቃላይ

## 1.1 መግቢያ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግስት በሃገሪቷ  ፈጣንና ዘላቂነት ያለው ልማት ለማረጋገጥና ማህበራዊ ደህንነትን ለማስፈን የሚያስችሉ የተለያዩ ልማታዊና ማህበራዊ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን ቀርጾ በሁሉም የአገሪቱ ክልሎች እንዲተገበሩ በማድረግ የሚያበረታቱ ውጤቶችን እያስመዘገበ ይገኛል፡፡ ከማህበራዊ ዘርፎች አንዱ በሆነው በጤና ሴክተርም ህብረተሰቡ ጤናው ተጠብቆ በልማት ሂደቱ በሙሉ አቅሙ ተሳታፊ ሊሆን የሚያስችል ጤናማ እና አምራች ዜጋን ለማፍራት፤ በዚህም ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እድገት በሃገሪቷ ለማረጋገጥ አዲስ የጤና ፖሊሲ ቀርፆ ለተግባራዊነቱም ያላሰለሰ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

የጤና ፖሊሲው ከሃገሪቷ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ጋር ተጣጥሞ ሊፈጸም የሚችል፤ በዋናነት በሽታን በመከላከልና ጤናን በማጐልበት ላይ እንዲያተኩር ተደርጎ የተቀረፀ ነው፡፡ ፖሊሲውን ለመተግበር የሚያስችሉ ሴክተር አቀፍ እስትራቴጂዎች እና አራት የአምስት ዓመት የልማት እቅዶች ተቀርፀው እንቅስቃሴ ውስጥ የተገባ ሲሆን እስከ አሁን ባለው ጊዜ ሁለት የአምስት አመት የጤና ሴክተር የልማት እቅድ ምዕራፎች ተፈፃሚነት አግኝተው በአሁኑ ጊዜ ሦስተኛው ምዕራፍ በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡ከሁለተኛው ምዕራፍ የጤና ሴክተር ልማት ስትራቴጂክ ዕቅድ ጀምሮ በሁሉም የሃገሪቷ የገጠር ወረዳዎች በትግበራ ሂደት ውስጥ ያለው የገጠር ጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ ነው፡፡ የፖኬጁ ዋና ዓላማ ከጤና ተቋማት ርቆ የሚገኘውን የህብረተሰብ ክፍል የመሰረታዊ ጤና አገልግሎት ተጠቃሚ ለማድረግና የጤና አገልግሎቱን ስርጭት ፍትሃዊነት ለማረጋገጥ በዚህም የጤና ፖሊሲውን ዓላማና ግቦች ለማሳካት ነው፡፡ ይህ ፖኬጅ ሃገሪቷ እንድታሳካ የሚጠበቅባትን የምዕተ-ዓመቱ የልማት ግቦች በተፋጠነ ጊዜና ወጭ ቆጣቢ በሆነ አኳኋን ለማስፈፀም ውጤታማነቱ ከመረጋገጡም በላይ የህብረተሰቡን ጤና ከማጎልበትና በሽታን ከመከላከል አንጻር በሃገር አቀፍ ደረጃ ብዙ ተሞክሮዎች የተገኙበት ነው፡፡

የፌደራል ጤና ጥበቃ ሚ/ር በአገራችን ከተሞች ያለውን የጤና አገልግሎት የተደራሽነት ችግር ለመቅረፍ በገጠር ወረዳ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አፈጻጸም የተገኙ ተሞክሮዎችና አመርቂ ውጤቶችን አንድ ላይ በመቀመር እና

በአገራችን ከተሞች ያለውን ተጨባጭ የጤና አገልግሎት ችግሮች ከከተማው ህብረተሰብ አኗኗር ጋር በማዛመድ እንዲሁም ከአገራችን ጋር የተቀራረበ እድገት ደረጃ ካላቸው ሃገሮች የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ልምዶችን በመቅሰም እነሆ በሦስተኛው የጤና ሴክተር ልማት ምዕራፍ የሚተገበር የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ ቀርጸዋል፡፡ የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ ዓላማም በዋናነት በፈውስ ህክምና ላይ ተንጠልጥሎ የሚገኘውን የከተማ የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት ፖሊሲው በሚያዘው መሰረት መልሶ በማዋቀር በከተማ በሽታን የመከላከልና ጤናን የማጎልበት አገልግሎቶች ተቋማዊ አደረጃጀት እንዲኖራቸው ማድረግ ነው፡፡ በተጨማሪም በከተማ ጤና አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት ውስጥ የሚስተዋለውን የከተማው ህብረተሰብ ካለው የግንዛቤ እጥረትና በኢኮኖሚያዊ አቅም ማነስ ምክንያት ከመሰረታዊ ጤና አገልግሎት ተጠቃሚነት የመራቅ ችግር ለመፍታትና የከተማው ህብረተሰብ በሚኖርባቸው አካባቢዎች በተፋጠነ ጊዜ የመሰረታዊ ጤና አገልግሎት ተጠቃሚ የሚሆንበትና ጤናውን ራሱን በራሱ ማምረት የሚችልበትን ሁኔታ የመፍጠር ዓላማ ያለው ነው፡፡ ይህም ማለት በነዋሪዎች ሙሉ ተሳትፎ በከተሞች የሚታየውን የግልና የአካባቢ ንፅህና ጉድለት፣ ተስማሚ የመኖሪያ ቤትና የንፁህ ውሃ አቅርቦት እጥረት፣ የጤና ግንዛቤ ማነስ፣ የምግብ ማነስና አለመመጣጠን፣ የማህበራዊ ጠንቆች መስፋፋት፣ እንዲሁም ከአመጋገብ፣ ከሥራ ሁኔታ ጋር የተያያዙ ተላላፊም ሆነ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች በሕብረተሰቡ ጤና ላይ የሚያደርሱትን ጉዳት ለመግታት የሚያስችል ፓኬጅ ነው፡፡

በአዲስ አበባ ከተማችንም በህዝብ ቁጥር ፈጣን እድገትና ከዚሁ ጋር ተያይዞ በተከሰቱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች እንዲሁም 34 በመቶ ባልዘለለ የጤና አገልግሎት ሽፋን እና በመሰረታዊ ልማት ተቋማት አለመሟላት ምክንያት በነዋሪው ህይወትና ምርታማነት ላይ እያደረሰ ያለው ጉዳት በቀላሉ የሚገመት አይደለም፡፡ አዲሱ የከተማችን አስተዳደር በዘርፉ ስር ነቀል ለውጥ ለማምጣት እየሠራቸው ካሉ ተግባራት አንዱና ዋነኛው የአዲስ አበባን የጤና ዘርፍ ልማት ማቀላጠፍ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ሁለት አቅጣጫዎችን የተከተለ እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል፡፡ አንደኛው አቅጣጫ ስርነቀል የማስፈፀም አቅም ግንባታ በማካሄድ ዘርፉን በአሠራሩ፣ አደረጃጀቱና አመለካከቱ መቀየር ነው፡፡ በዚህም በሁሉም የአስተዳደሩ የጤና ዘርፍ እርከኖች ላይ መሠረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት አካሂዶ እየተገበረ ይገኛል፡፡ የጤና አገልግሎቱ ተደራሽና ህብረተሰቡን የሚያረካ እንዲሆን ሰፊ ጥረት

እየተደረገ ነው፡፡ ለውጥም መታየት ጀምሯል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ሁለተኛው አቅጣጫ ደግሞ የሀገራችንን የጤና ፖሊሲና ስትራቴጂ ማዕከል በማድረግ የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ኘሮግራምን አስተሳስሮ የመፈፀም ጉዳይ ልዩ ትኩረት አግኝቷ፡፡ የከተማዋ ጤና ቢሮ በህብረተሰቡ ጤና ላይ የሚደርሰውን ጫና ለመግታት ያስችላል ተብሎ በፌደራል ጤና ጥበቃ ሚ/ር የተቀረጸውን "የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን የአተገባበር ማንዋል" ከከተማዋ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ለከተማችን አመራር ፖኬጁን ለመምራት በቂ ግንዛቤ ሊያስጨብጥ በሚችል መልኩ "*የከተማው ጤና ኤክስቴንሽን ረቂቅ የማስፈጸሚያ ሰነድ*" አዘጋጅቶ በከተማው አስተዳደር ካቢኔ ውሳኔ እንዲሰጥበት አድርጓል፡፡

የከተማ ጤና አክስቴንሽኑ የህዝቡን ሁለንተናዊ ችግሮች ለመፍታትና የህዝብ ተገልጋይነትን ለማረጋገጥ የዘርፉ የመሰረታዊ የአሰራር ሂደት ለውጥ (BPR) አንድ አካል ሆኖ በመላው ህብረተሰብ ተሳትፎና በከተማዋ አመራር በቂ ግንዛቤ ላይ በተመሰረተ ልዩ ክትትልና ድጋፍ ተፈጻሚነት እንዲያገኝ ጤና ቢሮው ያቀረበውን የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ የማስፈጸሚያ ረቂቅ ሰነድ አጽድቋል፡፡ በዚህም በየደረጃው ያለው የከተማዋ አመራር የፕሮግራሙን ጠቃሚነት በመረዳት በልዩ ፖለቲካዊ ቁርጠኝነትና ቀጣይነት ባለው ክትትልና ድጋፍ ማስፈጸም ይጠበቅበታ፡፡

## 1.2 ትርጓሜ

1. "የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ" ማለት በአዲስ አበባ ከተማ የሚኖረውን ህብረተሰብ ጤና ለማጎልበትና ከበሽታዎች ለመከላከል የሚያስችሉ የመሰረታዊ ጤና አገልግሎቶችን በኤክስቴንሽን ኘሮግራምና ንዑስ ኘሮግራሞች መልክ በማደራጀት በቤተሰብ፣ በከተማ መኖሪያ አካባቢዎች፣ በትምህርት ቤቶችና በወጣት ማዕከላት ደረጃ እንዲሁም ከከተማው ልዩ ባህርይ አንፃር ወደፊት በሚለዩ ሌሎች አስፈላጊ ቦታዎች ፕሮግራሙን ለማስፈጸም ተመልምለው በሰለጠኑ ባለሙያዎች በመታገዝ ተግባራዊ የሚሆን ፕሮግራም ሲሆን ዓለማውም ጤናማ ህብረተሰብና ጤናማ የመኖሪያና የስራ አካባቢዎችን በከተማዋ በሚገኙ ሁሉም ክፍለ ከተሞች ለመፍጠር ነው፡፡
2. "**መሰረታዊ** የጤና አገልግሎት" ማለት የህብረተሰብ ጤናን ለማበልፀግና ከበሽታ ለመከላከል የሚያስችሉ የሐይጂንና የአካባቢ ጤና አጠባበቅ፣ የቤተሰብ ጠ

ና ክብካቤ፣ የበሽታዎች መከላከልና መቆጣጠር፣ የጉዳትና ግጭት መከላከልና የመጀመሪያ ደረጃ ሕክምና እርዳታና የሕሙማን አላላክና አቀባበል አገልግሎቶችን የሚያጠቃልል ነው::

3. "የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ" ማለት ከመንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ያልሆኑ ወይም የግል ጤና ሳይንስ ኮሌጆች በክሊኒካል ወይም በማህበረሰብ ነርስ ሙያ በዲፕሎማ ተመርቀው በክ/ከተማ ጤና ጽ/ቤት አማካኝት የተመለመሉና በከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ጠኬጆች ላይ በዳግማዊ ሚኒሊክ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከ3-4 ወራት ለሚደርስ ጊዜ በሞዲዩላር የማስተማሪያ ዘዴ ስልጠና የተሰጣቸው ወይም በአስተዳደሩ ጠፍ ቢሮ ተቀባይነት ባለው ዘዴ በጉዳዩ ላይ የንድፈ ሀሳብና የተግባር ልምምድ የወሰዱ ሴት ነርሶች ናቸው::

4. "የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ ሱፐርቫይዘር" ማለት በአካባቢ ጤና ሙያ ወይም በነርስ ወይም በጤና አጠባበቅ ትምህርት ባለሙያ ወይም በሌሎች የጤና ዘርፎች በዲፕሎማ ወይም በዲግሪ ተመርቆ/ተመርቃ የተቀመጠው የስራ ልምድ ያለው/ያላት የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን ለማስተባበርና ለመምራት ፍላጎትና ተነሳሽነት ያለው/ያላት በከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ሱፐርቫይዘርነት ስልጠና የተሰጠው/የተሰጣት ለኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ቴክኒካዊ ድጋፍ የሚሰጥ/የምትሰጥና የምታስተባብር ባለሙያ ነው/ናት ::

5. "የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ ቡድን" ማለት የጤናና የኤች.አይ.ቪ. መከላከልና መቆጣጠር ስራዎችን በወረዳ ደረጃ ለማስተባበር በጽ/ቤት ደረጃ የሚዋቀር ሆኖ በወረዳው ጤና ጣቢያ ካለ እና በቂ ቦታ ካለው በጤና ጣቢያ ውስጥ፣ ወረዳው ጤና ጣቢያ ከሌለው ወይም ጤና ጣቢያ በቂ ቦታ ከሌለው ግን በጊዚያዊነት አመች በሆነ የወረዳ ኤክስቴንሽን ማዕከል ውስጥ የሚደራጅ ቡድን ሲሆን የሚመራውም በአካባቢ ጤና ባለሙያ ወይም በነርስ ወይም በጤና አጠባበቅ ትምህርት ባለሙያ ወይም በጤና መኮንን ወይም በሌሎች የጤና ዘርፍ ባለሙያዎች የሆነና ጤና የማበልፀግና በሽታን የመከላከል አገልግሎትን በቤተሰብና በመኖሪያ አካባቢ፣ በት/ቤትና በወጣት ማዕከል ለመስጠት በሰለጠኑ የሴት የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችን ያካተተ ነው::

6. "ሞዴል ቤተሰብና የመኖሪያ አካባቢ" ማለት በከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችና በግንባር ቀደም የጤና ተባባሪዎች አማካኝነት የጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጆችን በቤተሰብና በመኖሪያ አካባቢ በመተግበራቸው በሞዴልነት የተመረጡ እና የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅን በጐረቤት ቤተሰቦች ውስጥ እንዲተገበሩ

በማድረግ ጤናማ ቤተሰብና የመኖሪያ አካባቢ ለመፍጠር ተነሳሽነት ያላቸው ቤተሰብ እና የመኖሪያ አካባቢዎች ናቸው::

7. "የትምህርት ቤት ጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ" ማለት በከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችና በግንባር ቀደም የጤና ተባባሪዎች አማካኝነት ጤናማ የት/ቤት ህብረተሰብ እንዲሁም የመማሪያና የስራ አካባቢን በትምህርት ቤቶች ውስጥ ለመፍጠር ታስቦ ተዘጋጀ የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ፓኬጅ ነው::

8. "የወጣት ማዕከል ጤና ኤክስቴንሽን " ማለት በከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችና በግንባር ቀደም የጤና ተባባሪዎች አማካኝነት በየወጣት ማዕከል ውስጥ ተግባራዊ የሚደረግ የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ጠኬጅ ሲሆን አላማውም ጤናማ ወጣቶችንና የወጣት ማዕከላትን ለመፍጠር እንዲያስችል ታስቦ የተቀረጸ ፕሮግራም ነው::

9. "ግንባር ቀደም የጤና ተባባሪዎች" ማለት በሚኖሩበት ህብረተሰብ ወይም ማህብረሰብ ውስጥ፣በመልካም ስነ-ምግባራቸው፣ በለውጥ ተቀባይነታቸውና አራማጅነታቸው በነዋሪውና በጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ የተመሰከረላቸውና የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን ለመደገፍና ለማራመድ ፈቃደኛ ሆነው በጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ ተመርጠው የሰለጠኑና ፓኬጆቹ በሚተገበሩባቸው አካባቢዎች ሁሉ አጋዥ ሆነው ለመንቀሳቀስ ዝግጁነታቸውን ያሳዩ እና ወደ ትግበራ የዘለቁ የህብረተሰብ ክፍል ናቸው::

10. "የህብረተሰብ ተሳትፎ" ማለት ሕብረተሰቡ በራሱ ጥረት የራሱን ጤና ለማምረት በሚያስችለው አኳኋን የተቀረጸውን የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ከማቀድ፣መተግበር እስከ ክትትል የዘለቀ የሕብረተሰቡ እንቅስቃሴዎችን የሚያጠቃልል ሲሆን ሕብረተሰቡ በግሉ ወይም በራሱ ባደራጃቸው ማህበራት አማካኝነት በጉልበት፣ በዕውቀት፣ በቁሳቁስና በገንዘብ አስተዋጽኦ ሊገለፁ የሚችሉ ዙሪያ መለስ እንቅስቃሴዎችን በባለቤትነት ማጠርከት ነው::

11. "ቅንጅታዊ አሠራር" ማለት የከተማዋን ነዋሪ ጤናን ለመንከባከብና ከበሽታ ለመከላከል ብሎም የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ዓላማና ግቦችን ለማሳካት ጤና ሴክተሩ ከሌሎች ሴክተሮችና የልማት አጋሮች ጋር በፕሮግራሙ አፈፃፀም ሂደት ማን ምን ይሥራ፣ መቼና የት ይሥራ በሚሉ ጉዳዩች ላይ በጋራ በመወሰንና ያላቸውን ሃብት፣ መረጃና ልምድ ለመጋራትና በትብብር ለመንቀሳቀስ የሚያስችላቸው የተዘረጋ አሰራር ማለት ነው::

12. "የወረዳ የጤና ኮሚቴ" ማለት የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን በወረዳው ለመተግበር በሙሉ ፈቃደኝነት ጊዜያቸውን አቅማቸውንና እውቀታቸውን ለማበርከት ሙሉ ፈቃደኛ የሆኑ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን እና ፕሮግራሙ ከሚመለከታቸው ሴክተር መስሪያ ቤቶች የተወከሉ ከ5-9 አባላትን የያዙ በወረዳው አስተዳደር የሚዋቀር ኮሚቴ ነው፡፡

## 1.3 የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ ዓላማ

### 1.3.1 አጠቃላይ ዓላማ

በቤተሰብ፣ በመኖሪያ አካባቢ፣ በትምህርት ቤቶችና በወጣት ማዕከላት እንዲሁም ከአዲስ አበባ ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር በስራ ቦታና ዕድሮች እንዲሁም የወጣትና ሴት ፎረሞችና በማሳሰሉ ማህበራዊ አወቃቀሮች አማካኝነት መሰረታዊ የጤና አገልግሎት ፕሮግራሞችን ለህብረተሰቡ በተፋጠነና ፍትሃዊ በሆነ ሁኔታ በማዳረስ ጤናማ አምራች፣ ቤተሰብና ጤናማ የስራና የመኖሪያ አካባቢዎችን መፍጠር፤

### 1.3.2 ዝርዝር ዓላማዎች

1. ሕብረተሰቡን በመኖሪያ አካባቢ፣ በትምህርት ቤትና በወጣት ማዕከላት በማደራጀት ነዋሪው በራሱ የጤና ጉዳይ ውሳኔ የሚሰጥበትና የራሱን ጤና በራሱ እንዲያመርት ማስቻል፣
2. ንቃተ-ጤናን በህብረተሰቡ በሰፊው በማስረጽ እያንዳንዱ ነዋሪ ስለ ጤናው ያለው አመለካከትና የአኗኗር ባህሪ የተሻለ ጤና ሊያጎናጽፈው የሚችል እንዲሆን በማድረግ ጤናው የተጠበቀ ጤናማና አምራች ህብረተሰብ መፍጠር፤
3. በኅብረተሰቡ ግንባር ቀደም ተሳትፎ በቅንጅታዊ አሰራር በጠንካራ የፖለቲካ አመራር በህዝባዊ ንቅናቄ ጤናን የማጎልበትና በሽታን የመከላከል ፕሮግራሞች ተፈጻሚነት እንዲያገኙማድረግ፤
4. በከተማችን መሠረታዊ የጤና አገልግሎት ሽፋንና ጥራትን በማሳደግ ሕብረተሰቡን መሰረት ያደረገ የጤና አገልግሎት የህሙማን አላላክና አቀባበል ሥርዓትን የተሟላ ማድረግ፣

5. የትምህርት ቤት ጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን ተግባራዊ በማድረግ በከተማችን ጤናማ የት/ቤት ህብረተሰብ እንዲሁም ጤናማ የትምህርትና የስራ አካባቢዎችን መፍጠር፤
6. በወጣት ማዕከላት ጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን ተግባራዊ በማድረግ በከተማችን ጤናማ ወጣቶችና የወጣት ማዕከላት መፍጠር፤

### 1.3.3 የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ ግቦች

1. የእናቶችን ጤና ክብካቤ አገልግሎት በማጠናከር በከተማዋ የሚደርሰውን የእናቶች ሞትና ህመምን በከፍተኛ ደረጃ መቀነስ፤
2. የህጻናትን ጤና ክብካቤ አገልግሎት በማጠናከር በከተማዋ የሚደርሰውን የህጻናት ሞትና ህመምን በከፍተኛ ደረጃ መቀነስ፤
3. የበሽታ መከላከል ፕሮግራሞችን በተጠናከረ ሁኔታ በመፈጸም ቲቢና ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በሽታዎች ህብረተሰቡ ላይ የሚያደርሱትን ሞትና ህመም በከፍተኛ ደረጃ መቀነስ፤
4. የአካባቢ ጤና አጠባበቅ አገልግሎትን በማጠናከር በከተማችን ጤናማ የስራና የመኖሪያ አካባቢዎችን መፍጠር፤
5. የጉዳትና ግጭት መከላከልና የመጀመሪያ ደረጃ ሕክምና እርዳታን በህብረተሰብና በቤተሰብ ደረጃ ተግባራዊ በማድረግ ህብረተሰቡ ላይ የሚደርሰውን ሞትና አካል ጉዳት በከፍተኛ ደረጃ መቀነስ፤
6. የሕሙማን አላላክና አቀባበል ስርዓትን የተሟላ በማድረግ በህብረተሰቡ የሚደርሰውን የህክምና አገልግሎት አሰጣጥ እንግልት በመቀነስ የአገልግሎት ስርዓቱን የተሳለጠ ማድረግ፤

## 1.4 የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ መሰረታዊ ፍልስፍና

በሰለጠኑ የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች እና በግንባር ቀደም የጤና ተባባሪዎች አማካኝነት የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም መልእክቶችንና ተግባራትን ወደያንዳዱ ቤተሰብ፤ ት/ቤትና ወጣት ማዕከላት እንዲሁም ሌሎች የሥራና ማህበራዊ ተቋሞችና አደረጃጀቶች በማድረስ የቤተሰብንና

የማህበረሰብን ንቃተ-ጤና ማሳደግ፤ አወንታዊ የጤና አመለካከቶች በእያንዳዱ ግለሰብ ዘንድ እንዲዳብር ማድረግ እና ነዋሪው በተሰማራበት የስራ ዘርፍ ምርት እንደሚያመርተው ሁሉ የራሱን ጤና በራሱ ጥረት እንዲያመርት ማስቻል ነው፡ ፡

## 1.5 የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ አፈጻጸም ስልቶች

የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ በከተማው ጤና ሴክተር እየተተገበረ ካለው የመሰረታዊ ስራ ሂደት ለውጥ አንዱ አካል እንደመሆኑ መጠን ከዚህ በፊት በጤና ሴክተሩ የነበረውን የተደራሽነት፤ የህብረተሰብ አሳታፊነትና የአገልጋይነት ችግርን ሊፈቱ ይችላሉ ተብለው በተለዩ ስልቶች የሚተገበር ይሆናል፡፡ ስልቶቹም፤

1. ሕብረተሰቡ የራሱን ጤና ችግር በመለየትና ቅደም ተከተሉን ለይቶ መፍትሄውን በማስቀመጥም ሆነ በመተግበር ግንባር ቀደም ተሳታፊ እንዲሆን ማስቻል፤ ተሳትፎውንም ማጠናከርና ማጎልበት፣
2. በየደረጃው ያለው የከተማው አመራር ለፕሮግራሙ መሳካት ተገቢውን የፖለቲካ ቁርጠኝነት ማሳየት፤ ቀጣይነት ያለው ድጋፍ እና ክትትል ማድረግ፣
3. በፕሮግራሙ አፈጻጸም የሚመለከታቸው መንግስታዊ ተቋማት መካከል ቅንጅታዊ አሰራርን ማስፈን፡፡ ፕሮግራሙ በቅንጅትና በሚደጋገፍ ሁኔታ የሚሰራበት የሚያስችላቸው የመግባቢያ ሰነድና አሰራር በማዘጋጀት ወደ ትግበራ መግባት፣
4. መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ የልማትና በጎ አድራጎት ድርጅቶችን ተሳትፎ ማጠናከር ለፕሮግራሙ ማስፈጸሚያ የሚሆን ሃብትን ማሰባሰብና የተገኘውን ሃብት አሟጦ መጠቀም፣
5. ከነዋሪው ህብረተሰብ ከት/ቤት ማህበረሰብ እና ከወጣት ማዕከላት ግንባር ቀደም

   የጤና ተባባሪዎችና ሞዴል ቤተሰቦችን መስፈርቶችን በመጠቀም መመልመልና

በእነርሱ አማካኝነት ፕሮግራሙ ሁሉም ህብረተሰብ ዘንድ በፍጥነት እንዲዳረስ

ማድረግ፤

6. በጤና ሴክተሩ የግልጸኝነትና የተጠያቂነት አሰራርን በማስፈንና በጤና ሴክተር አመራርና ባለሙያዎች የተነሳሽነትንና የአገልጋይነት አመለካከትን በማረጋገጥ ለፕሮግራሙ አፈጻጸም ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፣
7. የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን በዘላቂነት መደገፍ የሚያስችል የግብአት አቅርቦት ሥርዓት መፍጠርና ማጠናከር/ በሰው ኃይል፣ በቁሳቁስ፣ በገንዘብ፣ ወዘተ/ ፣
8. በከተማዋ ለጤና ኤክስቴንሽን ቴክንካዊ ድጋፍ የሚሰጡ የጤና ተቋማትንና ማሰልጠኛ ማዕከላትን ማጠናከር ፣
9. የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችን የሙያ ብቃት የሚያጎለብቱ ተከታታይ ስልጠናዎች ማካሄድ ፣
10. አሳታፊ የሆነ □ድጋፋዊ ክትትልና የግምገማ ሥርዓትን ማጠናከር ፣

## ምዕራፍ ሁለት

## የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ ይዘትና አደረጃጀት

### 2.1 በአዲስ አበባ ከተማ የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት አደረጃጀት

የፌደራል ጤና ጥበቃ ያስቀመጠው ስታንዳርድ እንደሚያመለክተው በከተማ የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት በሶስት እርከኖች እንደሚደራጅ የሚጠይቅ ሲሆን በከተማችንም ይህንኑ አደረጃጀት መተግበር ጠቃሚነቱ የጎላ ነው፡፡ በዚህ መሰረት፡-

1. የመጀመሪያ እርከን የጤና አገልግሎት የሚሰጠው በጤና ጣቢያዎች ውስጥ ሆኖ እያንዳንዱ ጤና ጣቢያ ከ25000 እስከ 40000 ህዝብ ያገለግላል፡፡ ይህም በአብዛኛው የከተማዋ ወረዳዎች ካላቸው ህዝብ ቁጥር ጋር የሚመጣጠን በመሆኑ በሚቀጥሉት አራት ዓመታት ወረዳዎች አንዳንድ ጤና ጣቢያዎች እንዲኖሯቸው እቅድ ተይዟል፡፡

2. የሁለተኛ እርከን ጤና አገልግሎት የሚሰጠው እስከ 50 ታማሚዎችን በአንድ ጊዜ የማስተኛት አገልግሎት መስጠት በሚችሉ ጠቅላላ ሆሲፒታሎች ውስጥ ሲሆን በፌደራል ጤና ጥበቃ ባስቀመጠው ስታንዳርድ አንድ ጠቅላላ ሆስፒታል ከ250,000 እስከ 400,000 ህዝብ ያገለግላል፡፡ ይህም አብዛኛው ክ/ከተሞች ካላቸው የህዝብ ቁጥር ጋር የሚመጣጠን በመሆኑ አንድ ጠቅላላ ሆስፒታል በእያንዳንዱ ክ/ከተማ እንዲኖር መደረግ ይኖርበታል፡፡

3. ሦስተኛ እርከን የጤና አገልግሎት የሚሰጠው በአምስቱ ክልላዊ ስፔሻላይዝድ ሪፈራል ሆሲፒታሎች ይሆናል፡፡ እነዚህም ሆስፒታሎች አራቱን መሰረታዊ የህክምና ዘርፎች ማለትም የውስጥ ደዌ፣ ማህጸንና ጽንስ፣ ህጻናትና አጠቃላይ ቀዶ-ጥገና ህክምና በተሟላ ሁኔታ ሊሰጡ በሚችሉበት ሁኔታ እንዲደራጁ መደረግ ይኖርበታል፣

ከዚህ በፊት በከተማችን የነበሩ ክሊኒኮችና ጤና ኬላዎች እንደ መጀመሪያ ጤና አገልግሎት መስጫ ተቋም ሲያገለግሉ የቆዩ ሲሆን ከከተማ ጤና ኤክስቴንሽን የትግበራ ሂደት አኳያ ክሊኒኩ ወይም ጤና ኬላው በቂ ቦታ ካለውና በወረዳው ውስጥ ጤና ጣቢያ ከሌለ ወደ ጤና ጣቢያ የሚያድጉበት፣ በወረዳው ውስጥ ጤና

ጣቢያ ካለ ግን ስራቸውን እንደሚያቆሙና እንደሚታጠፉ ታሳቢ ተደርጓል፡፡ የወረዳው ተጨባጭ ሁኔታ የሚያስገድድ ከሆነ ጤና ጣቢያ ተገንብቶ ስራ እስከሚጀምር በጊዜያዊነት በከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ማዕከልነት ጥቅም ላይ የሚውልበት ሁኔታ ሊታይ ይችላል፡፡ ክሊኒኮችና ጤና ኬላዎች በመጀመሪያ ደረጃ የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋምነት እንዳይቀጥሉ የተወሰኑባቸው ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

1 የከተማዋ የጤና ችግሮች ውስብስብነት፤ የድንገተኛ አደጋዎች መበራከት፤

2 ህዝቡ በአነስተኛ ቦታ ተጠጋግቶ ስለሚኖር ተላላፊ በሽታዎች በቀላሉ ሊዛመቱበት የሚችሉ መሆኑ፤

3 ጤና ኬላዎችና ክሊኒኮች የተወሳሰቡ የከተማ ጤና ችግሮች መፍትሄ ለመስጠት የሚያስችላቸው የሰው ሃይል፤ አሰራር፤ አደረጃጀትና የአገልግሎት ማዕቀፍ ያልተፈጠረላቸው መሆናቸው፤

4 ከከተማችን ህብረተሰብ ጋር በተደረገ ውይይት ነዋሪው በአቅራቢያው ሁሉን አቀፍ የጤና አገልግሎት (Comprehensive Health Service) የሚሰጥ ተቋም እንደሚፈልግ በተደጋጋሚ በመገለፁና ይህንኑ የህብረተሰብ ጥያቄ መልስ ለመስጠት ጭምር ነው፡፡

በነዚህ ምክንያቶች በከተማችን ጤና ጣቢያዎች የመሰረታዊ ጤና አገልግሎት መስጫ የመጀመሪያ ተቋም ሆነው እንዲደራጁና በውስጣቸውም የህክምና አገልግሎቶች ከመስጠታቸው በተጓዳኝ በቤትና በማህበረተሰብ ደረጃ የጤና ማጎልበትና በሽታን መከላከል አገልግሎት መስጠት የሚያስችላቸው የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ቡድን በውስጣቸው እንዲደራጅ በካቢኔው ውሳኔ ላይ ተደርሷል፡፡ ይሁንና በሁሉም ወረዳ የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም እስኪጀምርና በአብዛኛው ወረዳዎች ጤና ጣቢያዎች ተገንብተው ስራ እስኪጀምሩ ድረስ የሽግግር ጊዜ መርሃ-ግብር ማውጣት አስፈላጊ መሆኑ ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ በሽግግር

ጊዜ ነባር ክሊኒኮችና ጤና ኬላዎች በወረዳው አስገዳጅ ሁኔታ ከሌለ በስተቀር በስራ ላይ መቆየት እንደሚችሉ ተወስኗል፡፡

## 2.2. በአዲስ አበባ የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን አደረጃጀት

- በከተማችን ጤና ሴክተር በተጠናው የመሰረታዊ የአሰራር ሂደት ለውጥ አኳያ የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ኘሮግራም በከተማና በክ/ከተማ ደረጃ ለመተግበርና ለመምራት እንዲቻል በጤና ቢሮና በክ/ከተማ ጤና ጽ/ቤት ወሳኝ የስራ ሂደቶች አንዱ በሆነው  የጤና ማጎልበት እና በሽታ መከላከል ውስጥ በንዑስ የስራ ሂደት ደረጃ እንዲዋቀር ተደርጓል፡፡
- ወረዳዎች የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ ዋናው የትግበራ ማዕከል በመሆናቸው  የኘሮግራሙን ዓላማ ለማሳካትና ጠንካራ አመራር ለመስጠት እንዲቻል የወረዳ ጤና ጽ/ቤቶች የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ እና የጤና ኤክስቴንሽን ሱፐርቫይዘሮችን በማቀፍ በአዲስ መልኩ እንዲኸቀር □ሳቤ ተጁ□ል፡፡
- የፌደራል ጤና ጥበቃ ባስቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት አንድ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ በአንድ አካባቢ ለሚኖሩ 500 ቤተሰቦች (በከተማችን እንደ ወረዳው የህዝብ አሰፋፈር ከ2000-2500 ሕዝብ) የቤት ለቤት አገልግሎት ለመስጠት እና አገልግሎት በምትሰጥበት ንዑስ ወረዳ በሚገኙ በመኖርያ አካባቢና በቤተሰብ፣ ትምህርት ቤቶችና ወጣት ማዕከላት እንዲሁም ከከተማው ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር በስራ ቦታ እና ማህበራዊ አደረጃጀቶች ጭምር አገልግሎት መስጠት ይጠበቅባታል፡፡ ለዚህም የከተማችን ወረዳዎች ካላቸው የነዋሪ ህዝብ ብዛታ አንጻር በአማካይ 15 የኤክስቴንሽን ባለሙያ መመልመል ሲጠበቅባቸው በድምሩ በከተማችን 1468 የኤክስቴንሽን ባለሙያዎችን መመልመል ማሰልጠንና መቅጠር ይጠበቅብናል (ዝርዝሩን አባሪ ከተያያዘው ሰንጠረዥ  ይመልከቱ)፡፡
- ይሁንና የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች አመዳደብ የቤተሰብና የህዝብ ብዛት ማስረት ማድረጉ እንደተጠበቀ ሆኖ በወረዳዎችና በንዑስ ወረዳዎች ያለው የማስረተ-ልማት ዝርጋታ፣የህብረተሰብ የኢኮኖሚ ደረጃ፣የአሰፋፈር ጥግግት እና የማሳሰሉ ሁኔታዎችን ከግንዛቤ ወስጥ በማስገባት የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችን ምደባ ማስተካከል ይቻላል፡፡ ይህ ማለት ሰፊ ህዝብ ጭቅንቅ

ያለበት ንዐስ-ወረዳ ወይም ሰፈር በተነጻጻሪ በርከት ያለ ባለሞያ ቁጥር ሊመደብ ይችላል፡፡

- የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችን ለማገዝና ለመምራት ከ2-3 የጤና ኤክስቴንሽን ሱፐርቫይዘር በየቀበሌ ጤና ጽ/ቤቱ መመደብ ሲኖርባቸው በድምሩ በከተማችን 223 የኤክስቴንሽን ሱፐርቫይዘሮች ማሰልጠንና መመደብ ይኖርብናል (ዝርዝሩን አባሪ ከተያያዘው ሰንጠረዥ ይመልከቱ)::
- የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ □መ□መሪጸ እርከን የጤና አገልግሎት አሰጣጥ አንድ አካል በመሆኑ አደረጃጀቱም በቀበሌው ውስጥ ባሉ ጤና ጣቢያዎች ውስጥ መሆኑ ተመራጭነት ይኖረዋል:: ይሁንና ጤና ጣቢያው ካለው የቦታ ጥበት ወይም በየንዐስ ወረዳው የተመደበው የኤክስቴንሽን ባለሞያ ብዛት አንጻር በወረዳና በንዐስ ወረዳ ደረጃ የከተማ ኤክስቴንሽን ሜከል ሜደራጀትና የፕሮግራሙ ፈጻሚ ባለሞዎች መመደብ ሊታዩ ይችላሉ፡፡
- የጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ ሱፐርቫይዘር ወረዳ □ስዓ □ሚቆኘውን ጤና ጣቢያ ማዕከል በማድረግ የሚንቀሳቀስ ሲሆን ተጠሪነቱም በቴክኒክ ጉዳዩች ለጤና ጣቢያው ነው:: ወረዳው ውስጥ ጤና ጣቢያ ከሌለ በቴክኒክ ጉዳዮች ተጠሪነቱ ለክፍለ ከተማው ጤና ጽ/ቤት ሲሆን አስተዳደራዊ ጉዳዩችን በተመለከተ ተጠሪነቱ ለወረዳ ጤና ጽ/ቤት ነው::
- ከዚህ በተጨማሪ በወረዳው ውስጥ ከሚገኙ የሴክተር መስሪያ ቤቶችና ከልማት አጋሮችና ከተለያዩ የህብረተሰብ አካላት የተውጣጡ 5-9 አባላት የያዘ የወረዳ ጤና ኮሚቴ መመደብ ይኖርበታል:: ኮሚቴውም ፖኬጁን በበላይነት የማስተባበር፣ የመከታተል፣ ተገቢውን ድጋፍም የመስጠትና አፈፃፀሙን የመከታተልና ወቅታዊ የሆነ እርምጃ የመውሰድ ኃላፊነት አለበት::

## 2.3 በአዲስ አበባ የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ አፈጻጸም ሂደት

የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥን ቀልጣፋና ውጤ□ማ ለማትረፅ የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ የተበደበችበትን ንዑስ-ወረዳና ሰፈር ከፍላ በማደራጀት ተግባርና ኃላፊነትዋን መወጣት ይጠበቅባታል፡፡ ለዚህም ይረዳት ዘንድ ከንዑስ ወረዳ- ቿ ግንባር ቀደም የጤና ተባባሪዎችን በመመልመልና በማሰልጠን ፖኬጁን ከነሱ ጋር ትተገብራለች፡፡ ትከታተላለች፡፡ በአፈፃፀም ሂደት ግንባር ቀደም የጤና ተባባሪዎቹ ተጠሪነታቸው ለጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ ሲሆን፣ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ደግሞ ለከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ ሱፐርቫይዘር/ቡድን መሪ/ ነው፡፡

የጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ ሱፐርቫይዘር/ ቡድን መሪ/፣የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችና የግንባር ቀደም የጤና ተባባሪዎች በወረዳው የጤና ኮሚቴ በመታገዝ በተለያዩ አካባቢዎች የሚሰጡ የጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጆችን በተቀናጀ መልኩ እንዲተገበሩና ሕብረተሰቡ ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

የጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ አፈፃፀምን ለመከታተልና ወቅታዊ የሆነ እርምጃ ለመውሰድ ግንባር ቀደም የጤና ተባባሪዎች ከጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ጋር በየሣምንቱ በመደበኛ መልኩ አመቺ በሆነ ቦታ በመገናኘት በአፈፃፀም ላይ የጋራ ውይይት ያደርጋሉ፤ ተሞክሮዎችንም ይለዋወጣሉ፡፡ በተመሣሣይ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችም ከጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ ሱፐርቫይዘር/ ቡድን መሪ ጋር በየሳምንቱ በመሰብሰብ የአፈፃፀም ግምገማ ያደርጋሉ፡፡ የጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ ሱፐርቫይዘር /ቡድን መሪም/ ከወረዳው የጤና ኮሚቴ ጋር በየወሩ በመሰብሰብ በዕቅድ አፈፃፀም ላይ የጋራ ግምገማ ያካሂዳል፤ ለጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችም ግብረ መልስ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡

የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ፣ የጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ ሱፐርቫይዘር/ቡድን መሪ/፣ ግንባር ቀደም የጤና ተባባሪዎች፣ የወረዳው ጤና ጽ/ቤት ኃላፊና የወረዳው ጤና ኮሚቴ በወረዳው ዋና ስራ አስፈፃሚ ሰብሳቢነት በየወሩ በወረዳው የጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ አፈፃፀም ላይ ግምገማ ማካሄድ ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 2.4 የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ ይዘት

የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ ፤ ከከተማው ህዝብ አኗኗር አሰፋፈርና የአመጋገብ ስርዓት ጋር የተያያዙ ዋና ዋና የጤና ችግሮችን በዘለቄታዊነት ለመከላከልና የህብረተሰቡን ጤና ለማጎልበት በሚያስችል መልኩ እንዲደራጅ የተደረገ ሲሆን ይዘቱም በአራት የጤና ማጎልበትና የበሽታ መከላከል አበይት ፕሮግራሞች ስር የሚጠቃለሉ ከ15 ያላነሱ ንዑስ ፕሮግራሞችን ያቀፈ ነው፡፡

እነርሱም፡-

ሀ. የሐይጂንና የአካባቢ ጤና አጠባበቅ ፕሮግራም

1. የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ንዑስ ፕሮግራም፣
2. የግልን ንጽህናና የመኖሪያ አካባቢ ጤና አጠባበቅ ንዑስ ፕሮግራም፣
3. የምግብና ውሃ ንጽህና አጠባበቅ ንዑስ ፕሮግራም፣
4. የመፀዳጃ ቤት አያያዝና አጠቃቀም ንዑስ ፕሮግራም፣

ለ. የቤተሰብ ጤና ክብካቤ ፕሮግራም

5. የእናቶችና ህፃናት ጤና አጠባበቅ ንዑስ ፕሮግራም፣
6. የክትባት ንዑስ ፕሮግራም፣
7. የወጣቶች ስነ-ተዋልዶ ጤና ንዑስ ፕሮግራም፣
8. የቤተሰብ ዕቅድ ንዑስ ፕሮግራም፣
9. የሥነ-ምግብ ንዑስ ፕሮግራም፣

ሐ. የበሽታዎች መከላከልና መቆጣጠር ፕሮግራም

10. የወባ መከላከያና መቆጣጠሪያ ንዑስ ፕሮግራም፣
11. የቲቢና ሥጋ-ደዌ በሽታዎች መከላከያና መቆጣጠሪያ ንዑስ ፕሮግራም፣
12. የኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ንዑስ ፕሮግራም፣
13. ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች መከላከያና መቆጣጠሪያ ንዑስ ፕሮግራም፣
14. የአእምሮ ጤና አጠባበቅ ንዑስ ፕሮግራም፣

መ. የጉዳትና ግጭት መከላከልና የመጀመሪያ ደረጃ ሕክምና እርዳታና የሕሙማን አላላክና አቀባበል ፕሮግራም፣

ከ15ቱ ንዑስ ፕሮግራሞች በተጨማሪ የጤና አጠባበቅ ትምህርትና (IEC) በሽታዎች ቅኝት እንደ ፓኬጁ ማስፈጸሚያ ዋና መሣሪያነት ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡

## 2.5 የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ ምልመላና ስልጠና

## 2.5.1 የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ ምልመላ

የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ምልመላ የሚካሄደው በክ/ከተማ ጤና ጽ/ቤት ኃላፊ የሚመራና ጉዳዩ የሚመለከታቸው መንግስታዊ መስሪያ ቤቶችና የየወረዳው አስተዳደር በተቀያሪ አባልነት የሚሳተፉባቸው የምልመላ ኮሚቴዎች ሲሆን የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ ምልመላ መስፈርቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. ከመንግስትም ሆነ ከግል ኮሌጆች በህብረተሰብ ወይም በክሊኒካል ነርስነት በዲፕሎማ የተመረቁ ሴት ነርሶች፤
2. የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጁ በሚተገበርበት ወረዳ ውስጥ ነዋሪ የሆነች ይህ ካልተቻለ የክፍለ ከተማው ነዋሪ የሆነች፤
3. ከላይ ከተጠቀሰው በተጨማሪ፡-
   - ባለሙያዋ በመንግስት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ላይ የጠራ አመለካከት ያላት፤
   - ሕብረተሰቡን ማዳመጥ የሕዝብ ወገናዊነትንና ተቆርቋርነትን በሥራ ማሳየት የምትችል፣
   - ለለውጥና ለውጤት ለመሥራት ዝግጁ የሆነች፣
   - የሕብረተሰብን ወግ፣ ልምድና ባህል የምታከብር፣
   - ሕዝብ እምቅ የሆነ አቅም እንዳለው በመረዳት ከእቅድ እስከ ክንውን ድረስ በማሳተፍ ፕሮግራሙን በባለቤትነት እንዲመራ ማድረግ የምትችል፣
   - ከሴክተር መሥሪያ ቤቶች ጋር በቅንጅትና በቡድን የመሥራት ፍላጎት ያላት፣
   - ከሁሉም በላይ ጤናን በማበልፀግና በሽታን በመከላከል በጤናው ዘርፍ ከፍተኛ ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል የምታምን፣ ሌላውንም ለማሳመንና ዝግጁ የሆነች፡፡

## 2.5.2 የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ ስልጠና

በከተማችን የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ዋነኛው ስልጠና የሚካሄደው በዳግማዊ ምንሊክ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ውስጥ ሲሆን ስልጠናውም የንድፈ-ሃሳብ

ትምህርትን በኮሌጁ ካገኙ በኋላ በተመደቡበት ወረዳ በሚያደርጉት የመስክ ልምምድ የተደገፈ ይሆናል፡፡የስልጠናውም ቆይታ 3 ወራት ይሆናል፡፡ ከተማችን የሚያስፈልጋትን 1468 የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ለማሰልጠን በሁለት ዙሮች ሆኖ በእያንዳንዱ ዙር እስከ 740 ተመልማዮችን የሚያካትት ይሆናል፡፡

## 2.5 የከተማ የጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ የሚተገበርባቸው ሥፍራዎች

የጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ የአገልግሎት አሰጣጥ ከሌሎች የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ዘዴዎች የሚለየው የአገልግሎት አሰጣጡ ከተቋሙ ወደ ሕብረተሰብ አቀፍ (Community Based) መለወጡ ነው:: ይኸውም ሕብረተሰቡ አገልግሎት ለመፈለግ ወደ ጤና ተቋም ሳይሄድ አገልግሎቱ በጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችና ግንባር ቀደም የጤና ተባባሪዎች አማካኝነት በቤቱና በአካባቢው ላይ ሆኖ የራሱን ጤና ራሱ እንዲያመርት የሚደረግበትና ሕብረተሰቡ ወደሚኖርበት አካባቢ በመሄድ መሠረታዊ የጤና አገልግሎቶችን እንዲያገኝ የሚያደርግ የአሠራር ሂደትን መከተሉ ነው::

በከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅን በከተሞች ለመተግበር የተመረጡት ዋና ዋና ስፍራዎች ሶስት ሲሆኑ እነሱም፡-

1. ቤተሰብና መኖሪያ አካባቢዎች
2. ትምህርት ቤቶች
3. ወጣት ማዕከላት ናቸው:: የስራ ቦታዎች እና ማህበራዊ አደረጃጀቶችና ተቋሞችም በተከታይነት ትኩረት የሚገኙ ናቸው፡፡

እነዚህ ስፍራዎች የተመረጡበት ምክንያት በከተማችን የሥራና የአኗኗር ዘይቤ መሠረት ሕብረተሰቡ የሚኖርባቸው ወይም በስፋት የሚገኝባቸው ስለሆኑና ለስራና ለተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች አብዛኛውን ጊዜውን የሚያሳልፍባቸው በመሆናቸው ነው፡፡ እናም ስፍራዎቹን ለህብረተሰቡ ጤና ተስማሚ በሚሆን መልኩ ማደራጀቱ አስፈላጊነቱ የሚያጠያይቅ አይደለም:: በነዚህ አካባቢዎች የሚኖሩና የሚሰሩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ያሏቸው የጤና ፍላጐቶችና ችግሮች በተወሰነ ደረጃ የተለያዩ በመሆናቸው የአገልግሎት አሰጣጡም እንዲሁ የተለያዩ አገልግሎቶችን

በማካተት የሕብረተሰቡን የጤና ፍላጐት ለማርካት በሚያስችል መልኩ እንደሚከተለው ተደራጅቶ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

**ሠንጠረዥ-1፡ የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ ንዑስ ኘሮግራሞች የሚተገበሩባቸው ሥፍራዎች**

| ተ.ቁ | ንዑስ ኘሮግራሞች | በቤተሰብና በመኖሪያ አካባቢ | በትምህርት ቤት | በወጣት ማዕከላት | *በአ.አ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሌሎች መንግስታዊ ተቋማት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ንዑስ ኘሮግራሞች | ሀ | ሀ | ሀ | ጽዳትና ውበት ኤጀንሲ<br>የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን |
| 2. | የግል ንጽህናና የመኖሪያ አካባቢ ጤና አጠባበቅ ንዑስ ኘሮግራሞች | ሀ | ለ | ለ | ድንብ ማስከበር |
| 3. | የምግብና ውሃ ንጽህና አጠባበቅ ንዑስ ኘሮግራሞች | ሀ | ሀ | ሀ | ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ<br>የወኃና ፍሳሽ ባለስልጣን |
| 4. | የመፀዳጃ ቤት አሠራር፣ አያያዝና አጠቃቀም ንዑስ ኘሮግራሞች | ሀ | ሀ | ሀ | የአካባቢ ልማት ጽ/ቤት |
| 5. | የእናቶችና የህፃናት ጤና አጠባበቅ ንዑስ ኘሮግራሞች | ሀ | ለ | ለ | የሴቶች ጉዳይ ቢሮ<br>የተለያዩ የሴቶች ፎረሞች |
| 6. | የክትባት ንዑስ ኘሮግራሞች | ሀ | ለ | ለ | |
| 7. | የወጣቶች ሥነ-ተዋልዶ ጤና አጠባበቅ ንዑስ ኘሮግራሞች | ሀ | ሀ | ሀ | ውጣቶችና ስፖርት ቢሮ<br>የሴቶች ጉዳይ ቢሮ<br>የተለያዩ የወጣቶች ፎረሞች |
| 8. | የቤተሰብ ዕቅድ ንዑስ ኘሮግራሞች | ሀ | ሀ | ሀ | የሴቶች ጉዳይ ቢሮ<br>የተለያዩ የሴቶች ፎረሞች |
| 9. | የሥነ-ምግብ ንዑስ ኘሮግራሞች | ሀ | ለ | ለ | |
| 10. | የወባ መከላከያና መቆጣጠሪያ ንዑስ ኘሮግራሞች | ሀ | ለ | ለ | |
| 11. | የቲቢና ሥጋደዌ መከላከያና መቆጣጠሪያ ንዑስ ኘሮግራሞች | ሀ | ሀ | ሀ | |
| 12. | የኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ንዑስ ኘሮግራሞች | ሀ | ሀ | ሀ | የኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ መከ/መቆ/ጽ/ቤት |
| 13. | ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች መከላከያና መቆጣጠሪያ ንዑስ ኘሮግራሞች | ሀ | ለ | ለ | |
| 14. | የአእምሮ ጤና ንዑስ ኘሮግራሞች | ሀ | ሀ | ሀ | |
| 15. | የጉዳትና ግጭት መከላከልና የመጀመሪያ ደረጃ ሕክምና ዕርዳታ እና የሀሙማን አላላክና አቀባበል ንዑስ ኘሮግራሞች | ሀ | ሀ | ሀ | -የአ.አ እሳትና ድንገተኛ አደጋዎች መከ/መቆ/ኤጀንሲ<br>-የአ.አ ትራፊክ ጽ/ቤት<br>-መንገድ ትራንስፖርት |

| | | | | | -የአ.አ ቀይ መስቀል ጽ/ቤት |
|---|---|---|---|---|---|

*መግለጫ* :- ሀ ፡ ንዐስ ኘሮግራሙሙሉ በሙሉ የሚተገበርበት

ለ ፡ ንዐስ ኘሮግራሙበተወሰነ ደረጃ የሚተገበርበት

- **የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ ዓላማዎችን በአዲስ አበባ ለማሳካት የበርካታ የአስተዳደሩ መንግስታዊ ተቋማትን ቅንጅታዊ አሰራርና ርብርብ ስለሚጠይቅ የሚመለከታቸው አካላት የተጣለባቸውን ሃላፊነት** መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡
- ለከተማው ጤና ኤክስቴንሽን ትግበራ ከተሚጠቅ 3 ስራዎች በተጨማሪ የወረዳው ወይም ንዐስ ወረዳው ያለበት ተጨባጭ ሁኔታ የሚያስገድድ ከሆነ በተለይም በስራና በተለያዩ ምክንያት የሚደረስባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ካሉ የሰፈሩ ነዋሪ የሚገለገልባቸው ዕድሮችና ሌሎች ማህበራዊ አወቃቀሮች ለምሳሌ የነዋሪዎች የወጣቶች ሴቶች ፎረም ማህበራትና ሊጎች ለፕሮግራሙ ቅስቀሳና ማስፈጸሚያ መድረኮች ጥቅም ላይ ሊወሉ ይችላሉ፡፡
- በነዚህ ጥረቶችም የሚደረሱ የህብረተሰብ ክፍሎች እንዳሉ ከተገመተ የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሞያዎች ቤተሰብ /ህብረተሰብ በሞሪያው አካባቢ የሚገኝበትን የእረፍት ቀናት በማጠቀም አገልግሎት እንዲሰጡ ይጠበቅባቸዋል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

# የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ አተገባበር

## 3.1 በወረዳ ደረጃ የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ አጠቃላይ የሥራ ሂደት ፍሰት

ሕብረተሰቡ ጤናውን ጠብቆ ለመኖር የሚያስችል መረጃ በማግኘት ዕውቀቱንና ክህሎቱን ማዳበር እንዲችል በቅድሚያ የሚከናወነው የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያን ከወረዳው አመራርና

ከጤና ጣቢያ፤ ከሴክተር መሥሪያ ቤቶች፣ ከብዙኃን ማህበራት፣ ከልማት አጋሮችና ከሕብረተሰቡ ጋር እንዲተዋወቁ የሚድረግ ጉዳይ ነው፡፡ ከዚያም የወረዳውን የጤና ችግሮችና ችግር ፈቺ መፍትሔዎችን በመለየት ዕቅድ ማዘጋጀት ይገባል፣ እቅዱ ተዘጋጅቶ በወይይት ከዳበረ በኋላ በሶስቱ ዋና ዋና ስፍራዎች ወደ ተግባር ይገባል፡፡ በዚህም መሠረት የሞዴል ቤተሰብና የመኖሪያ አካባቢ እቅድን በመተግበር የራሱን ጤና ያመረተ ቤተሰብና ጤናማ የመኖሪያ አካባቢ እንዲኖር የማድረግ፣ በት/ቤት የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅን በመተግበር ጤናማ የትምህርት ቤት ህብረተሰብና ጤናማ የመማሪያና የሥራ አካባቢ እንዲኖር የማድረግ እንዲሁም በወጣት ማዕከላት የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅን በመተግበር ጤናማ የሆኑ በርካታ ወጣቶች የመፍጠር ስራ ይከናወናል፡፡

## 3.2 የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ የስራ ሂደት ፍሰት ዝርዝር ተግባራት

### 3.2.1 ሕብረተሰቡንና አካባቢዋን ጠንቅቃ የማወቅ አጠቃላይ የስራ ሂደት ፍሰት

ይህ የትውውቅ ተግባር ባለሙያዋ ወደ መደበኛ ስራዋ ከመግባቷ በፊት ስለሕብረተሰቡና አካባቢዋ ጠንቅቃ በማወቅ ወደ ሥራ በምትሰማራበት ጊዜ ምን እንደምታከናውን ግልጽ የትኩረት አቅጣጫ ይዛ የጋራ የሥራ ግንኙነትን በመፍጠር የጋራ ዓላማን ለማሳካት እንድትችል ይረዳታል:: የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ፓኬጅን ለማራመት የሚከተለውን የሥራ ሂደት ፍሰት ይከተላሉ፣

- ሕብረተሰቡንና አካባቢዎን በቅድሚያ የማወቅ፣ ቀጣይ ሥራ ለመስራትም አላቆታቸውን መረዳት፣
- ከቀበሌ አመራርና ከጤና ጣቢያ ጋር ትውውቅ ማድረግና የሥራ ግንኙነት ፍሰቱን ማመቻቸት፣
- ከሴክተር መሥሪያ ቤቶች ከብዙሀን ማህበራት፣ ከልማት አጋሮችና ከሕብረተሰብ ጋር የጋራ ሥራን ለመሥራት መተዋወቅ እና ሥራቸውን እንዲያውቁ ማትረፅ፣ ጁኸውም በአጠቃላይ ከሕብረተሰቡ ጋር በተናጠል በመወያየት ስለ ወረዳው ጤና ገጽታ፣ ጤና ነክ ኘሮግራሞች፣ የአፈፃፀም ሥርዓት፣ በወረዳ ስለሚገኝ ሀብት / የሰው ኃይል፣የቁሳቁስና የገንዘብ/ እንድያወቁ ያደርጋቸዋል:: ስለአካባቢው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ሁኔታዎች ለመገንዘብ ይረዳ ዘንድ በሕብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ካላቸው ታዋቂ ግለሰቦችና የሀይማኖት አባቶች፣ በአካባቢው ለረዥም ጊዜ ከኖሩና በወረዳው የበለጠ ግንዛቤ ካላቸው ግለሰቦች ጋር ጊዜ ሰጥቶ መወያየት

- ❖ ከጤና ኤክስቴንሽን መሪና ከጤና ባለሙያዎች ጋር ተጨማሪ ውይይት በማድረግ በሚከናወኑ ተግባራት ላይ የጋራ ግንዛቤ ለማፍጠር እንዲቻልና በጋራ ለመሥራት ስምምነት ላይ መድረስ፣

በስተመጨረሻም የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች አካባቢያቸውንና ሕብረተሰቡን ጠንቅቀው በዚህ መልክ የሚያውቁበት የሥራ ሂደት ፍሰት በተዋረድ ይፈጠራል፡፡

## 3.2.2. ሕብረተሰቡንና አካባቢዋን ለማወቅ የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት አፈፃፀም

### 3.2.2.1 ከወረዳና ከጤና ጣቢያ አመራሮች ጋር ትወወቅ ማድረግ

የጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ ተግባራዊነት በአብዛኛው በወረዳው ሕብረተሰብ ተሳትፎ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ ከወረዳው አመራር ጋር በቅድሚያ ትውውቅ ማድረግ ይኖርባታል፡፡ ይህ ሂደት በቀጣይ ሥራዋ ከአመራሩ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ለመፍጠር ከመርዳቱም ባሻገር ወደፊት በወረዳው ውስጥ ከሕብረተሰቡ ጋር በመግባባት ለመሥራትና የሕብረተሰቡን ተሳትፎና ድጋፍ ለማግኘት ያግዛታል፡፡
ከወረዳዉም ሆነ ከጤና ጣቢያው ኃላፊዎች ጋር የሚደረገው ግንኙነት ፖኬጅን ተግባራዊ በምታደርግበት ጊዜ ምን ድጋፍ እንደሚደርግላት ለመገንዘብና ከማን ጋር ግንኙነት ማድረግና በቅንጅት በመሥራት የጤናውን ልማት ለማፋጠን እንድምትችል ለማወቅ ያስችላታል፡፡ በተጨማሪ የስራ ትውውቁ ስለወረዳው ነዋሪ አጠቃላይ የጤና ሁኔታ የበለጠ ለመረዳት እንድትችል ስለሚያደርግ የሚኖራትን የሥራ ድርሻ የበለጠ እንድታውቅና በሥራ ሂደት ተግባርና ኃላፊነቷን ጠንቅቃ እንድታውቅ ይረዳታል፡፡

### 3.2.2.2 ከሕብረተሰቡና ከልማት አጋሮች ጋር ትውውቅ ማድረግ

የጤና ስራ የጤናው ሴክተር ብቻ ሳይሆን የሌሎችንም ሴክተሮች አስተዋጽኦ የሚጠይቅ በመሆኑ በልማቱ ድርሻ ያላቸው አካላት በቅንጅት መስራት ለወረዳው የጤና ልማት ወሳኝ ነው፡፡ በመሆኑም የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ በወረዳው ከሚገኙ የሴክተር መ/ቤቶች፣ በጤናው ዙሪያ ከሚንቀሳቀሱ የልማት አጋሮች፣ ከብዙኃን ማህበራት (የወጣቶች፣ የሴቶች፣ ዕድር፣ ወዘተ.) እና በአጠቃላይ ከሕብረተሰቡ ጋር በተናጠል በመወያየት ስለ ወረዳው ጤና ገጽታ፣ ጤና ነክ

ፕሮግራሞች፣ የአፈፃፀም ሥርዓት፣ በወረዳው ስለሚገኝ ሀብት (የሰው ኃይል፣ የቁሳቁስና የገንዘብ) እንድታውቅ ያደርጋታል።

#### 3.2.2.3 ከሱፐርቫይዘሯና ከጤና ባለሙያዎች ጋር ትውውቅ ማድረግ

የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ ተጠሪነቷ ለጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ ሱፐርቫይዘር /ቡድን መሪ ነው። በመሆኑም በቴክኒካዊ ጉዳዩች ረገድ በቅድሚያ ከፖኬጁ ሱፐርቫይዘር ጋር የምታደርገው ውይይት አስፈላጊውን መረጃና የስራ ድርሻዋን፣ የሪፖርት አዘገጃጀትንና አላላክን፣ የዕቅድ አስተቃቀድን፣ የስራ ግንኙነትን፣ የተለያዩ ፎርሞችንና ሰነዶች አጠቃቀምን፤ በአጠቃላይ ያላትን መብትና ግዴታ፣ ወዘተ. እንድታውቅ ይረዳል። በመሆኑም ከጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ ቡድን መሪ ጋር የምታደርገው የስራ ውይይት ተግባርና ኃላፊነቷን እንድትወጣ የሚያስችል ቁልፍ ተግባር ነው።

ከዚህ በተጨማሪ በጤና ጣቢያ ከሚሠሩ የተለያዩ ባለሙያዎች ጋር በመደበኛም ሆነ መደበኛ ባልሆነ መልኩ በምታደርገው መስተጋብር ስለአካባቢው የጤና ችግሮች፣ ስለሚወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች፣ ስለፖኬጁ አፈፃፀም፣ በወረዳው በጤናው ዘርፍ የሚሠሩ የልማት አጋሮችና ሴክተር መስሪያ ቤቶች ስላላቸው ተሳትፎ መረጃዎችን በማግኘት ለወደፊት ለምታደርጋው እንቅስቃሴ መሠረት በመሆን ይረዳል። በተጨማሪ በጤናው ሴክተር ከሚሠሩ የግልና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር ከወዲሁ ግንኙነት ለመፍጠር አሠራርና አደረጃጀት ለመገንዘብና የጋራ ዓላማን ለማሳካት የትውውቅ ፕሮግራሙ የላቀ ጠቀሜታ ይኖረዋል።

### 3.2.3. የጤና ችግሮችንና ችግር ፈቺ መፍትሔዎችን በመለየት እቅድ ማዘጋጀት

**ሀ/ አጠቃላይ መግለጫ**

የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ ዋና ዓላማ የወረዳው ሕብረተሰብ የራሱን የጤና ችግር በራሱ ተሳትፎ በመፍታት ጤናውን እንዲያመርት ማስቻል ነው። ተሳትፎውም በሚያደርገው የገንዘብ፣ የጉልበትና የቁሳቁስ ድጋፍ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን በእያንዳንዱ የአፈፃፀም እርከን ማለትም፡-

- ይወረዳውን አጠቃላይ የጤና ሁኔታ በመገምገም፣
- ዋና ዋና የጤና ችግሮችን በመግለጽ፣
- ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ለይቶ በማውጣትና ግብ በማስቀመጥ፣
- የድርጊት መርህ ግብር በማዘጋጀት፣
- ፕሮግራሙን ተግባራዊ በማድረግ፣
- ውጤትን በመከታተልና በመገምገም የነቃ ተሳትፎ ሲያደርግ ጭምር ነው::

በዋናነት የወረዳዉን ዕቅድ ለማዘጋጀት በቅድሚያ የወረዳዉን ካርታ ማዘጋጀት ከዚያም የመነሻ ጥናት / Base line survey/ ማካሄድ የተለያዩ ሠነዶችን መመርመር፣ እነዚህንም መሠረት በማድረግ መረጃዎችን በመተንተንና በማጠናቀር የወረዳዉን የጤና ገፅ□ / Health profile/ ማዘጋጀት ከዚያም የወረዳዉን ችግር ፈች ዓመታዊ ዕቅድ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን ታዘጋጃለች::

ለ/ የእቅድ ዝግጅት ስራ ሂደት ፍሰት

የወረዳዉን የጤና ችግሮችና ችግር ፈቺ መፍትሔዎችን የመለየትና እቅድ የማዘጋጀት ጉዳይ የሚከተለዉን ዝርዝር ሂደት ይከተላል፡ –

- የጤና መረጃ ማሰባሰብ፣
- የሕብረተሰቡን የጤና ችግሮች መዘርዘርና በቅደም ተከተል መለየት መተንተንና ማጠናቀር
- ስምምነት ላይ መድረስ
- ግልጽ ግቦች ያሉትን ዕቅድ በጋራ ማዘጋጀት
- የዕቅድ ማስፈፀሚያ ሀብት በቀበሌው አማካኝነት ማሰባሰብ
- የጤና ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል የተዘጋጀ የወረዳ እቅድ

## 3.2.4 በሞዴል ቤተሰብና የመኖሪያ አካባቢ የጤና ኤክስቴሽን ፖኬጅን መተግበር

### 3.2.4.1. አጠቃላይ መግለጫ

የቤተሰብና የመኖሪያ አካባቢ ለጤና ወሳኝ የሆኑ ጉዳዩች የሚፈፀሙበት ለምሣሌ □ምፅብ ዝግጅት፣ የውሀ አቅርቦት፣ ሕፃናት የሚያድጉበት የግልና የአካባቢ ንጽህና የሚጠበቅበት ወዘተ.. ነው:: በመሆኑም የተጠቀሱት ጉዳዬች በአኗኗር ምክንያት በቤተሰብና በአካባቢ ሕብረተሰቡ ጤና ላይ ጉዳት እንዳያስከትል ሆነው መደራጀት ይኖርባቸዋል ::

ቤተሰብ የሕብረተሰቡም ሆነ የራሱን ጤና ለመጠበቅ እና በአካባቢ ከሚገኙ ጐረቤቶች ጋር በመቀናጀት በመተግበርና በመረዳዳት በኘሮፅራሙ ላጁ □ሚጸስኖኛ

ው ውጤት ከፍተኛ ነው:: በተለይም የቦታ ጥበትና የአቅም ማነስ በመኖሩ ምክንያት ተፋፍገው በሚኖሩ ቤተሰቦች አካባቢ እያንዳንድ ቤተሰብ የራሱ የሆነ የቧንቧ ውሀ፣ የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ፣ ወዘተ... ላይኖሩት ስለሚችሉ እነዚህን አገልገሎቶች የአካባቢው ቤተሰብ በጋራ ማዘጋጀትና መጠቀም አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው:: ከዚህም በተጨማሪ ከየቤቱ ለሚወጡ ፍሳሽ ቆሻሻዎች መውረጃ በዩችን የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያና ማስወገጃዎችን የመፍትሄ □ርምጃ መ□ሰት ጴቆባል::

ለ□ህም ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት ተከታታይነት ያለው ችግር ፈቺና በተግባር የተደገፈ ሥልጠና እንዲያገኙ ማድረግና ተግባራዊነቱንም መከ□ተል ይኖርበ□ል:: የጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅን በመተግበር ሞዴል የቤተሰብና የመኖሪያ አካባቢ ለመፍጠር ከዚህ እንደሚከተለው በቅደም ተከተል ይፈፀሜ: -

- የአገልግሎት መስጫ ክልሏን በንዑስ ወረዳና በቀጠና በመከፋፈል ለሥራ ማደራጀት
- ሞዴል ቤተሰብና መኖሪያ አካባቢ ሰልጣኞችን መመልመል፣ የስልጠናን ሥፍራና ጊዜ መወሰን
- የስልጠናውን ስልት /ዘዴ መወሰን፣ የትምህርት ዕቅድ ማዘጋጀትና የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎችን ማሟላት
- በዕቅዱ መሠረት ስልጠናውን ለሞዴል ቤተሰቦች መስጠት
- 75% በተግባር የተረጐሙትን ሞዴል ቤተሰቦች ማስመረቅ
- ከተመረቁት መካከል የተሻለ ብቃትና ፍላጐት ያላቸውን በመመልመል በግንባር ቀደም የጤና ተባባሪነት እንዲያገለግሉ ማሰልጠን
- የግንባር ቀደም የጤና ተባባሪዎች ሥራቸውን ሲያከናውኑ ድጋፋዊ ክትትል ማድረግ
- በሞዴልነት የታቀፉ ቤተሰቦች ጤናማ ተግባራትን በዘላቂነት እንዲተገበሩ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ
- የተፈጠረ ጤናማ ቤተሰብና የመኖሪያ አካባቢ

### 3.2.4.2. በሞዴል ቤተሰብና የመኖሪያ አካባቢ የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት አፈፃፀም፣

ሀ. የአገልግሎት መስጫ ክልሉን በንዑስ ወረዳና በቀጠና በመከፋፈል ማደራጀት

ፖኬጁን ተግባራዊ ለማድረግ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ በቅድሚያ ማከናወን ያለባት በአገልግሎት መስጫ ክልልዋ የሚገኙትን ቤተሰቦችን በካርታው መሠረት በንዑስ-ወረዳ፣ በእድርና በማህበር የሚገ ኙትን መከፋፈል በክፍፍሉ መሠረት የቤተሰብ አባላት በጋራ በመወያየት ዕቅድ በማውጣት ሀብትና ጉልበታቸውን በማቀናጀት ለጋራ ጥቅም ለማዋል አመች ሁኔታዎችን ይፈጥራል፡፡ በዚህም መሠረት የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ ስብሰባ በማዘጋጀት ሕብረተሰቡ ውይይት እንዲያደርግ ታደርጋለች፡፡ የውይይቱም ሂደት በቅደም ተከተል እንዲሚከተለው ቀርቧል፡፡

- የቅድመ ውይይት መርሃ ግብር ከየንዑስ-ወረዳው ተጠሪዎችና ከዕድር አመራሮች ጋር በመሆን ማዘጋጀት፣
- ውይይቱን ከማካሄድ በፊት የውይይቱን አጀንዳ፣ ቀን፣ ጊዜና ቦታ መወሰን፣
- ሕብረተሰቡ በንዑስ-ወረዳ ወይም በእድር ማደራጀት ያለውን አስፈላጊነትና ጠቀሜታ ሕብረተሰቡ ግንዛቤ እንዲያገኝ ማድረግ፣
- በውይይቱ ጊዜ ስለአጀንዳው ማብራሪያ መስጠት፣
- በውይይቱ ጊዜ ተሳታፊዎች ተግባርና ኃላፊነታቸውን እንዲወጡና ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ማበረታታት፣
- የውይይቱን ፍሬ ሀሳቦች በማንሳት የማጠቃለያ ሃሳብ ማቅረብና የጋራ ውሳኔ ላይ መድረስ፣
- የውይይቱን ቃለ ጉባኤ ማዘጋጀት፣
- በውይይቱ የጋራ ውሳኔ ላይ የተደረሰባቸውን ጉዳዩች መተግበራቸውን መከታተል ናቸው፡፡

ለ. ሞዴል ቤተሰቦችን መመልመል፣ የስልጠናን ቦታና ጊዜ መወሰን

የሞዴል ቤተሰብና የመኖሪያ አካባቢ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን ተግባራዊ ለማድረግ ከሕብረተሰቡ መካከል በለውጥ አራማጅነታቸው አርአያ ለሆኑ ቤተሰቦች ቅድሚያ በመስጠት በጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋና በሕብረተሰብ ተወካዮች አማካኝነት ፍቃደኛ የሆኑ፣ ትምህርቱን ቶሎ የሚቀበሉ፣ ለለውጥ ዝግጁ የሆኑ፣ በሕብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነትና በልማት ሥራ ቶልህ ሚና ያላቸው ይመለመላሉ፡፡ ከዚያም የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ ከሰልጣኞች ጋር በመሆን ስልጠናው የሚሰጥበትን ቀንና ሰዓት እንዲሁም አፈፃፀሙን ቤት ለቤት በመሄድ ወይም በአንድ አመቺ ስፍራ እንዲሆን በጋራ ይወስናሉ፡፡

### ሐ. ለስልጠናው የሚያስፈልጉ ግብአቶችን ማሟላት

የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ ስልጠናውን ከመስጠቷ በፊት አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት ሁሉ ማድረግ ይገባታል፡፡ ይኸውም ይህንን የጤና ኤክስቴሽን ፖኬጅ አተገባበር መሜያ እና ፕሮግራሞቹን መሠረት በማድረግ የትምህርት ዕቅድ በማዘጋጀት ወደ ትግበራ ትገባለች፡፡

### መ. በሞዴል ቤተሰብ ሥልጠናን ማካሄድ

የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ አገልግሎት በምትሰጥበት የወረዳ □ልሏ □ስዓ ቁጥራቸው ከ500 ያላነሱ ቤተሰቦች በአንድ አመት ተኩል ጊዜ ውስጥ በሞዴል ቤተሰብና የመኖሪያ አካባቢ የጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ እንዲሰለጥኑ ታደርጋለች፡፡

### ሠ. ሞዴል ቤተሰቦችን ማስመረቅ

ለሞዴል ቤተሰብ ሰልጣኞች ስልጠና ከተሰጠው አጠቃላይ ጊዜ 75% እና ከዚያ በላይ ከተከታተሉና የተሰጠውን ትምህርት በተግባር ከተረጐሙ ለምረቃ ብቁ ይሆናሉ፡፡በዚሁ መሠረት ለምረቃ ብቁ መሆናቸውን የጤና ኤክስቴንሽን ሱፐርቫይዘር /ቡድን መሪ በግንባር በመገኘት ይህንኑ እንዲያረጋግጥ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ ጥያቄ ታቀርባለች፡፡ የጤና ኤክስቴንሽን ሱፐርቫይዘር /ቡድን መሪ ሰልጣኞች በንድፈ ሃሳብና በተግባር ያሳዩትን ብቃት የሚከተሉትን መስፈርቶች ተከትሎ በመገምገም ወጠቃሚ የሆኑትን ለምርቃ ብቁ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡

- የመፀዳጃ ቤት ማዘጋጀትና በአግባቡ መጠቀም፣
- የእጅ መታጠቢያ ከመጸዳጃ ቤት አጠገብ መኖርና መጠቀም፣
- የፍሳሽና ደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ማዘጋጀትና መጠቀም፣
- የግል ወይም የጋራ የገላ መታጠቢያ ማዘጋጀትና መጠቀም
- የውሃና የምግብ ንጽህና መጠበቅ፣
- የመኖሪያ ቤታቸውና አካባቢው ሲታይ ንጽሕናው የተጠበቀ ሆኖ ሲገኝ

- ከመኖሪያ የተለየ የምግብ ማዘጋጃ /ኩሽና/ ቤት መኖር፣
- የክትባት አገልግሎትን (ሕፃናትና እናቶች) ማጠናቀቅ፣
- የቤተሰብ ዕቅድ መጠቀም፣
- በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ የምክር አገልግሎትና የደም ምርመራ ማድረግ፣
- ወባማ በሆኑ አካባቢዎች አጐበርን መጠቀም፣
- ህፃናት እስከ ስድስት ወር ድረስ የእናት ጡት ወተት ብቻ ማጥባት፣

ከዚህ በተጨማሪ እያንዳንዱ ሰልጣኝ ቤተሰብ የወሰደውን ስልጠና አስመልክቶ ግንዛቤ መጨበ ጡን ለማመረጋገጥ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ ከሱፐርቫይዘሯ/ ቡድን መሪው ጋር በመሆን ከሁሉም ንዐሰ ኘሮግራሞቹ ጥያቄዎች ተዘጋጅተው የቃልና የጽሑፍ ፈተና ሰልጣኞች እንዲወስዱ ይደረጋል፡፡በዚሁ መሠረት ከ75% በላይ ያመጡ ሰልጣኞች ለምረቃ ብቁ ይሆናሉ፡፡ይህን ያላሟሉ ሰልጣኞች ግን ተጨማሪ የማጠናከሪያ ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጐ መስፈርቱን ሲያሟሉ ይመረቃሉ፡፡

## ረ. ግንባር ቀደም የጤና ተባባሪዎችን መመልመልና ማሠልጠን ፣

በወረዳው ክልል ውስጥ የሚገኙትን ቤተሰቦች በአጭር ጊዜ ውስጥ በቤተሰብና በመኖሪያ አካባቢ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ለማቀፍ በጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ አማካኝነት ከሚሰለጥኑት መካከል ግንባር ቀደም የጤና ተባባሪዎችን በመመልመልና በማሰልጠን መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡በመሆኑም በመጀመሪያ ዙር ከሰለጠኑት 60 ሞዴል የቤተሰብና የመኖሪያ አካባቢ አባላት መካከል የተሻለ ብቃትና ፍላጐት ያላቸውን በመምረጥ ተጨማሪ የአምስት ቀን ስልጠና በመግባቢያ ዘዴዎች፣ በመረጃ አያያዝና አጠቃቀም፣ በካውንስሊንግ፣ በማስተማሪያ ዘዴዎች፣ በትምህርት ዕቅድ ዝግጅት / Lesson Plan/ና በተግባርና ኃላፊነታቸው ላይ በጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ አማካኝነት ስልጠና ይሰጣቸዋል፡፡

# 3.2.5. በትምህርት ቤት የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ የስራ ሂደት ፍሰትና ዝርዝር አፈፃፀም

### 3.2.5.1 አጠቃላይ መግለጫ

ጤናማ ት/ቤትን ለማደራጀት የበርካታ መ/ቤቶችንና የሕብረተሰቡን ሙሉ ተሳትፎ የሚጠይቅ በመሆኑ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ ከነዚህ አካላት ጋር በመተባበር የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም በት/ቤት ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆን የሚጠበቅባትን አስተዋጽኦና ድጋፍ ታደርጋለች። ይህም ድጋፍ በአብዛኛው በአቅም ግንባታና በክትትል ላይ ያተኮረ ሲሆን በት/ቤት ውስጥ በዋናነት ፓኬጁን ተግባራዊ የሚያደርጉት ከት/ቤቱ ተመልምለው በግንባር ቀደም የጤና ተባባሪነት የሰለጠኑ መምህራን ናቸው።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ በት/ቤት በመተግበር ጤናማ የት/ቤት ሕብረተሰብና ጤናማ የት/ቤት አካባቢ ለመፍጠር የስራ ሂደት ፍሰቱ የት/ቤት የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅን ለመጀመር ከሚመለከታቸው ጋር ውይይት በማድረግና ስምምነት ላይ በመድረስ መጀመር አለበት፣ ከዚያም የሚከተሉት የሥራ ሂደት ተግባራት በቅደም ተከተል ሊፈፀሙ ይገባል፡ –

- ከመምህራን መካከል ፍላጐትና ችሎታ ያላቸውን በመመልመል በግንባር ቀደም  የጤና ተባባሪነት እንዲያገለግሉ ማሰልጠን
- ት/ቤቱ ጤናማ የመማሪያና የሥራ ቦታ እንዲሆን ለማድረግ አስተዋጽኦ ለሚያደርጉ አካላት የአድቮኬሲ ሥራ መሥራት
- የት/ቤቱ ግንባር ቀደም  የጤና ተባባሪዎች አገልግሎት ሲሰጡ ድጋፋዊ ክትትል ማድረግ
- በት/ቤቱ ውስጥ ለሚያጋጥመው ቀላልና ድንገተኛ ህመም የጤና ችግሮች የመጀመሪያ ደረጃ ህክምና ስልጠና መስጠትና መከታተል
- ፓኬጆችን መሠረት ባደረገ መልኩ በት/ቤት ውስጥ መደበኛ በሆነና በተቀናጀ መልኩ የጤና አጠባበቅ  ትምህርት እንዲሰጥ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ
- ከልማት አጋሮች፣  ከህ/ሰቡ፣ ወዘተ. ጋር በመሆን የት/ቤቱን አካባቢ ጠ ፡ናማ የማድረግ ሥራ መጀመር

በዚህም ጤናማ የመማሪያና የሥራ አካባቢ እንዲሁም ጤናማ የት/ቤት ሕብረተሰብ እንዲፈጠር ይደረጋል።

### 3.2.5.2 በትምህርት ቤት የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት

**አፈፃፀም**

ሀ/ ውይይት በማድረግ ስምምነት ላይ መድረስ

ትምህርት ቤት ከማይምነት የተላቀቀና አምራች ዜጋ የሚያፈራ እንደመሆኑ መጠን በከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ ላይ በስፋት እንዲሳተፍ ማድረግ ቁልፍ ተግባር ነው:: በትምህርት ቤት ውስጥ ቀደም ብሎ በጋራ የተዘጋጀውን ዕቅድ መሠረት በማድረግ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ ከት/ቤቱ ሕብረተሰብ ተወካዮች ጋር በመሆን የት/ቤት አገልግሎት መስጫዎች፣የመማሪያ ክፍሎች፣ የመፀዳጃ ቤት፣ የስፖርት ማዘውተሪያዎች፣ የመመገቢያ ቦታዎች፣የመጠጥ ውሃ፣የፍሳሽና የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃዎች፣ የቤተ-መፃህፍት አገልግሎት መስጫ ኪቶችን በተመለከተ ዳሰሳ በማድረግ ሰነድ ታዘጋጃለች::

የመጀመሪያ ደረጃ ሕክምና እርዳታ አሰጣጥን ተግባራዊ ለማድረግ ይረዳ ዘንድ በቅድሚያ አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት ማድረግ፣ የሚመለከታቸውን አካላት ለይቶ ማወቅ፣ የት/ቤት የጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅን ተግባራዊ ለማድረግ ከሚመለከታቸው የወላጆችና የመምህራን ኮሚቴ እንዲሁም ከወረዳው የጤና ኮሚቴ ጋር ውይይት ማድረግና ስምምነት ላይ መድረስ ይገባል:: አፈፃፀሙን በተመለከተም የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ፣ ከትምህርት ቤቱ ኃላፊዎችና መምህራን በጋራ በመሆን በዝርዝር ጉዳዩች ላይ በመወያየት የድርጊት መርሀ ግብር ያዘጋጃሉ::

ለ/ በግንባር ቀደም የጤና ተባባሪነት የሚያገለግሉ መምህራንን መመልመልና ማሠልጠን

በትምህርት ቤት ውስጥ ለሚካሄደው የት/ቤት የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ትግበራ የመምህራን ተሳትፎ የላቀ ነው:: በመሆኑም ከመካከላቸው ፍላጎት ያላቸው፣ በት/ቤቱ ህበረተሰብ ዘንድ አርአያ የሆኑ፣ በሌሎች ጤናና ጤናነክ ክበቦች ውስጥ የላቀ ተሳትፎ ያላቸውን በመመልመልና በት/ቤት ተግባራዊ በሚሆኑ ንዑስ ፕሮግራሞች ላይ በማሰልጠን የት/ቤቱ ግንባር ቀደም የጤና ተባባሪዎች ሆነው እንዲያገለግሉ ይደረጋል:: በት/ቤት ለሚሠሩ ግንባር ቀደም የጤና ተባባሪ መምህራን የሚሰጠው ስልጠና በመግባቢያ ዘዴዎች፣ በመረጃ አያያዝ፣ በመጀመሪያ ደረጃ ሕክምና አሰጣጥ፣ በህሙማን አላላክና አቀባበል፣በትምህርት ቤት ማህበረሰብ ውይይት በተግባርና ኃላፊነታቸው እንዲሁም በፕሮግራሞችና ንዑስ ፕሮግራሞች ላይ የአንድ ሳምንት ስልጠና በጤና

ኤክስቴንሽን ባለሙያዋና በሱፐርቫይዘሩ አማካኝነት ተሰጥቷቸው ይመረቃሉ፡፡ የምርቃቱ ሂደት ቀደም ሲል በቤተሰብና በመኖሪያ አካባቢ እንደተጠቀሰው ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ሐ/ የአድቮኬሲ ሥራ መሥራት

ከት/ቤቱ በግንባር ቀደም የጤና ተባባሪነት እንዲያገለግሉ ተመልምለው የሰለጠኑ መምህራን ፖኬጁ ውጤታማ እንዲሆን ከተማሪዎች መካከል ፍላጐትና ብቃት ያላቸውን በመመልመልና በማሰልጠን በት/ቤቱ ውስጥ አጋዥ ኃይል እንዲሆኑ ያደርጋሉ፡፡ ተማሪዎችም በት/ቤቱ ውስጥ በሚከናወኑት ጤናና ጤና ነክ ጉዳዮች ላይ የነቃና አርአያነት ያለው ተሳትፎ ከማድረግ ባሻገር በየቤታቸው የጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ ተግባራዊ እንዲሆን የበኩላቸውን ሚና ይጫወታሉ፡፡ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያና ት/ቤቱ የሴክተር መሥሪያ ቤቱ የወረዳው ተጠሪዎች፣ የወረዳ አመራሮች፣ የወረዳው

የጤና ኮሚቴዎች፣ የትምህርት ቤቱ የውተማህ አባላት፣ በሕብረተሰቡ ዘንድ የማሳመን ችሎታ ያላቸው ግለሰቦችና የሃይማኖት መሪዎችን በስብሰባ እንዲገኙ ያደርጋሉ፡፡ በስብሰባውም ጊዜ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ፡-

- በዳሰሳ የተገኙትን የት/ቤቱን ጤናና ጤና ነክ ችግሮችና የተዘጋጀውን ዕቅድ በግልጽ ተሳታፊዎች እንዲያውቁት ማድረግ፣
- ችግሩ ለተማሪዎች ጤናና ማህበራዊ ደህንነት ምን ያህል አሳሳቢ እንደሆነ ማሳየት፣
- ችግሩን በመፍታት ረገድ የት/ቤቱ ማህበረሰብና ሕብረተሰቡ የተሟላ አቅምና ችሎታ እንዳለው ማመላከት፣
- ከዚህ አንፃር የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብና ሕብረተሰቡ ችግሮችን ለመፍታት እንዲችሉ የሌሎች ሀገሮችን ተሞክሮ ማካፈል ፣
- ሌሎች መድረኮችንም በመጠቀም ለወረዳው አመራር አካላት፣ ለልማት አጋሮች፣ ወላጆችና ባለሙያዎች ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥተው የበኩላቸውን ድጋፍ እንዲያደርጉ ከትምህርት ቤት ኃላፊዎችና ግንባር ቀደም የጤና ተባባሪዎች ጋር በመተባበር የአድቮኬሲ ሥራ መሥራት ይጠበቅባታል፡፡

መ/ የትምህርት ቤት ሕብረተሰብና አካባቢን ጤናማ የማድረግ ተግባራትን መጀመር

ቀደም ሲል በተደረገው ስብሰባ ላይ በተሰጠው ተግባራዊ ምላሽ መሠረት የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ፣የት/ቤቱ ኃላፊዎችና ግንባር ቀደም የጤና ተባባሪዎች ከወላጆችና መምህራን ማህበር ጋር በቅንጅት በመሥራት በዕቅዱ መሠረት ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡ አፈፃፀሙን በተመለከተም ችግሩ መሠረታዊ በሆነ መልኩ እንዲፈታ ድጋፍ ላደረጉ አካላት በየወቅቱ ሪፖርት በት/ቤቱ በኩል እንዲደርስ ይደረጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ችግሩ ዘላቂ መፍትሔ እንዲያገኝ ላደረጉ ተባባሪ ግለሰቦችና ድርጅቶች የምስክር ወረቀት ተዘጋጅቶ ይሰጣቸዋል፡፡ ለዚህም ተግባራዊነት የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ ከተሜዎች፣ ከወላጆችና መምህራን ኮሚቴ እንዲሁም ከወረዳው የጤና ኮሚቴ ጋር በመሆን በጋራ መሥራትና መቀስቀስ ይኖርባታል፡፡

ሠ/ የጤና አጠባበቅ ትምህርት መስጠት

ት/ቤት በርካታ ተማሪዎችና መምህራን በአንድ ቦታ ተሰባስበው የሚገኙበት አካባቢ በመሆኑ ለተለያዩ ተላላፊ በሽታዎች መዛመት አመቺ ነው፡፡ ተማሪዎችም በአፍላ ዕድሜ ላይ ስለሚገኙ ለተለያዩ አደጋዎች የተጋለጡ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተማሪዎች የተሰጣቸውን በቀላሉ የሚቀበሉና የሚተገብሩ በመሆናቸው ጤናማ ባህሪ ይዘው እንዲያድጉ ለማድረግ ይቻላል፡፡ በመሆኑም በት/ቤት ለውጥ ለማምጣት በተቀናጀ መልኩ ፖኬጆችን መሠረት ያደረገ የጤና አጠባበቅ ትምህርት በት/ቤቱ ግንባር ቀደም የጤና ተባባሪዎች አማካኝነት መደበኛና ተከታታይነት ባለው መልኩ መስጠት ይገባል፡፡ የጤና አጠባበቅ ትምህርቱ በት/ቤቱ ውስጥ የተቋቋሙ የተለያዩ ክበቦችን፣ ሚዲያዎችን፣ የአቻ ለአቻ ፕሮግራሞችን፣ ወዘተ. በመጠቀም ይካሄዳል፡፡ የተጠቀሱት ክበባት የሚጠበቅባቸውን ውጤት ማምጣት እንዲችሉ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋና የግንባር ቀደም የጤና ተባባሪዎች አፈፃፀማቸውን በመገምገም ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡ በትምህርት ቤት የሚሰጠው የጤና አጠባበቅ ትምህርት ፖኬጆችን መሠረት በማድረግ በተለያዩ የጤና ርዕስ ጉዳዩች ላይ በማተኮር ሥዕላዊ መግለጫዎችን፣ ፍሊፕቻርቶችን፣ ሠርቶ ማሳያዎችን፣ በራሪ ወረቀቶችን፣ የኦዲዮቪዥዋል መሣሪያዎችንና የመሳሰሉትን በመጠቀም ይሰጣል፡፡

ረ/ የመጀመሪያ ደረጃ ህክምና እርዳታ ስልጠና መስጠት

በት/ቤቱ ውስጥ ተማሪዎች፣ መምህራንና ሌሎች ሠራተኞች የተለያዩ ህመምና አደጋ ሊያጋጥማቸው ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ በግንባር ቀደም የጤና ተባባሪነት እንዲያገለግሉ የሰለጠኑ መምህራን ለተከሰተው ችግር የመጀመሪያ ደረጃ ህክምና ይሰጣሉ፡፡ ችግሩ ከአቅማቸው በላይ ሆኖ ሲገኝ ግን ወደየጤና ጣቢያው በመላክ አገልግሎት እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ፡፡ ከዚህ ሌላ ተማሪዎች በትምህርት ገበታቸው ላይ እያሉ በተለያዩ ምክንያቶች / በሥነ-ልቦና፣ በምግብ ማነስ፣ በበሽታዎች፣ ወዘተ/ ምክንያት ትምህርታቸውን በተገቢው ሁኔታ መከታተል ሊሳናቸው ይችላል፡፡ እነዚህን ሁኔታዎች ግንባር ቀደም የጤና ተባባሪዎችና መምህራን በመከታተልና ሁኔታውን በመመዝገብ በቅድሚያ ወላጆችና አሳዳጊዎች እንዲያውቁና እገዛ እንዲያደርጉ ያደርጋሉ፡፡ ችግሩ ከወላጆችና አሳዳጊዎች አቅም በላይ መሆኑ ሲረጋገጥ የወረዳው አስተዳደር፣ የልማት አጋሮች፣ የት/ቤቱ ህብረተሰብና ሌሎች ድጋፍ እንዲያደርጉ ግንባር ቀደም የጤና ተባባሪዎችና የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ የበኩላቸውን ጥረት ያደርጋሉ፡፡

በት/ቤቱ ለሚገኙ ተማሪዎች በአመት አንድ ጊዜ መሠረታዊ የጤና ምርመራ / Screening/ በማድረግ የማየት፣ የመስማት፣ የመናገር ችግሮች ያለባቸውን በመለየት ችግሩ ከመባባሱ በፊት ከወላጆችና አሳዳጊዎች ጋር በመነጋገር የመፍትሔ እርምጃ እንዲወሰድ ትምህርት ቤቱ ከጤናው ሴክተር ጋር በመተባበር ጥረት ማድረግ ይገባዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በት/ቤቱ ውስጥ በሽታዎች በወረርሽኝ መልክ በመከሰት በት/ቤቱ ሕብረተሰብ ላይ የከፋ የጤና ችግር ከማድረሳቸው በፊት ት/ቤቱ ተገቢውን ክትትል በማድረግ አፋጣኝ የመፍትሔ እርምጃ መውሰድ ይጠበቅበታል፡፡ከዚህ አንፃር የት/ቤቱ ግንባር ቀደም የጤና ተባባሪ መምህራን የሚኖራቸው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ለምሳሌ በተመሳሳይ ወቅት የአንድ በሽታ ስርጭት ከፍ እያለ ሲመጣ ለምን ብሎ በመጠየቅ ችግሮቹን መለየትና ምንጩ ከቤተሰብ፣ ከሕብረተሰብ፣ ከት/ቤት መሆን አለመሆኑን ተከታትሎ በማወቅ ለሚመለከታቸው ሪፖርት በማድረግ አፋጣኝ መፍትሔ እንዲያገኝ ማድረግ ይጠበቃል፡፡በተመሳሳይ ተማሪዎች ከት/ቤት ሲቀሩ፣ የትምህርት መከታተል

ፍላጐታቸው ሲቀንስ፣ ወዘተ. ሁኔታዎችን በመከታተል የችግሮቹ መንስኤ በመመርመር መፍትሔ እንዲያገኝ ማድረግ ይገባል፡፡በእያንዳንዱ ተማሪ የግል ፋይል ውስጥ የጤናውን ሁኔታ የሚያሳይ መረጃ እንዲኖር ማድረግ ጠቃሚ በመሆኑ በት/ቤቱ ከተመዘገበበት ጊዜ ጀምሮ ያለውን የጤናውን ሁኔታ የሚገልጽ መረጃ እንዲሁም በየጊዜው የሚታየውን ለውጥና የተደረገ የህክምና እርዳታ መዝግቦ መያዝ ጠቃሚ ነው፡፡ ለዚህም የት/ቤቱ አስተዳደር ከጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋና ከግንባር ቀደም የጤና ተባባሪዎች ጋር በጋራ መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ሰ/ ለግንባር ቀደም የጤና ተባባሪዎች ድጋፋዊ ክትትል ማድረግ

የጤና ኤክስቴሽን ባለሙያዋ በሁለት ሳምንት አንድ ጊዜ በግንባር በመገኘት ድጋፍና ክትትል ማድረግ ይጠበቅባታል፡፡ በዚህም ወቅት የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ የግንባር ቀደም የጤና ተባባሪዎችን አፈፃፀም ለመገምገም በት/ቤቱ ቅጥር ግቢ በመዘዋወር የመፀዳጃ ቤት ንጽህናን፣ የምግብ ማዘጋጃና መመገቢያን፣ የመማሪያ ክፍሎችን ንጽህና፣ የፍሳሽና የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ፣ የውሃ አቅርቦትና ንጽህና አጠባበቅ፣ ወዘተ. በመመልከት መረጃ ትሰበስባለች፡፡

በተጨማሪ ዕቅድን ከክንውን ጋር በማነፃፀር በአፈፃፀም በኩል በታዩ ጠንካራና ደካማ ጐኖች ላይ ከግንባር ቀደሞች ጋር ውይይት በማድረግ የጋራ የመፍትሔ ዕርምጃ ለመውሰድ ስምምነት ላይ ይደርሳሉ፡፡ የዚህንም ሪፖርት የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ ለጤና ኤክስቴንሽን ሱፐርቫይዘር/ ቡድን መሪ አዘጋጅታ ታቀርባለች፡፡ በዚህ መልክ ት/ቤቱና የት/ቤት ሕብረተሰብ ጤናማ ሆነው የመማርና የማስተማሩ ሂደት ሳይደናቀፍ እንዲካሄድ ት/ቤቱ ጤናማ ት/ቤት ማሟላት ያለባቸው መስፈርቶች እንዲያሟላ ማድረግ ይጠበቃል፡፡

3.2.5.3 የጤናማ ት/ቤት መስፈርቶች

ት/ቤቶች ጤናማ ት/ቤት ተብሎ የሚሰየሙት የሚከተሉትን መስፈርቶች ሲያሟሉ ነው:-

ሀ. ንጹህና በቂ የመጸዳጃ ቤት ከእጅ መታጠቢያ ጋር ተዘጋጅቶና ለሴትና ለወንድ ተለይቶ ጥቅም ላይ ሲውል፣

ለ. የንጹህ ውሃ አቅርቦት ከት/ቤቱ ሕብረተሰብ አንፃር ተደራጅቶ ሲቀርብና

በየወሩ ኪት ምርመራ ሲደረግለት

ሐ. የደረቅና የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ተዘጋጅቶ ስራ ላይ ሲውልና የት/ቤቱ አካባቢ

ንጹህ ሲሆን፣

መ. ንጽህናቸው የተጠበቁና በቂ የብርሃን መጠን ያላቸው ተስማሚ የመማሪያ

ክፍሎች ሲኖሩ፣

ሠ. ለት/ቤቱ ሕብረተሰብ በቂ የሆነ የስፖርት ቦታ፣ የመዝናኛ ቦታ፣ የመመገቢያ

ክፍል፣ የመሰብሰቢያ አዳራሽ፣ የመምህራን ቢሮ ሲኖር፣

ረ. ለድንገተኛና ቀላል ጉዳቶች የመጀመሪያ ሕክምና ዕርዳታ መስጫ ኪት ተሟልቶ

ሲገኝ፣

ሰ. በጤና ጤና ነክ ጉዳዮች ላይ የተጠናከረ የክበባት ተሳትፎ (የትምህርታዊ

ጽሑፍ ዝግጅት፣ መልክቶችን በማሠራጨትና በመሳሰሉት) ሲኖር፣

ሸ. በወረዳው የጤና ልማት (በአረጋውያን ክብካቤ፣ በውሃ ማግኛ፣ በዘመቻ

ሥራዎች፣ ወዘተ.) የተማሪው ተሳትፎ የተጠናከረ ሲሆን፣

ቀ. የሴቶች ተሳትፎ በማደጉ የጾታዊ ትንኮሳና ጥቃት ሲቀንስና ሲወገድ፣

በ. በት/ቤቱ ለተማሪዎች የጤና ምርመራ /screening/ ሲደረግ

ይህም መሟላቱ በጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ አማካኝነት በቅድሚያ ፍተሻ ተደርጎ የጤና ኤክስቴንሽን ቡድን መሪ/ሱፐርቫይዘር በቦታው በግንባር ተገኝቶ በመገምገም ሲያረጋግጥ ነው፡፡

### በወጣት ማዕከል የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን መተግበር

#### 3.2.6.1 አጠቃላይ መግለጫ

ወጣቶች ራሳቸውን ከሚጐዱ ከአልኮል ሱሰኝነት፣ ከሲጋራ አጫሽነት፣ ከአደንዛዥ ዕፅ ተጠቃሚነት፣ ከውርጃ፣ ከኤች.አይ.ቪ/ ኤድስና ከአባላዘር በሽታዎች፣ ከስራአጥነት፣ ከወንጀለኛነት እንዲሁም ሕብረተሰቡን ከሚጐዱ ተግባራት ተጠብቀው ለሀገርና ለወገን መሥራት እንዲችሉ በትርፍ ጊዜያቸው እየተዝናኑ የሚማማሩበት ቦታ ማደራጀት አስፈላጊ ነው:: በመሆኑም በአሁኑ ጊዜ በተወሰኑ አካባቢዎች በወጣቶች፣ በሕብረተሰቡና በተለያዩ የልማት አጋሮች ተሳትፎ የወጣቶች ማዕከላት ተደራጅተው ለወጣቱ ጠቃሚ የሆኑ አገልግሎቶች በመስጠት ላይ ይገኛሉ::

በነዚህ የወጣቶች ማዕከላት ውስጥ ወጣቱን እያዝናኑ የሚያስተምሩ ተግባራት ይከናወናሉ:: እነዚህም ተግባራት የተለያዩ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች፣ የጤናና ጤና ነክ አገልግሎች፣ የገቢ ማስገኛ ፕሮግራሞች፣ ወዘተ. ናቸው:: በጤናው ዘርፍ የወጣቶች ስነ-ተዋልዶ ጤና፣ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስና ሌሎች አባላዘር በሽታዎች መከላከልና መቆጣጠር፣ የቤተሰብ ዕቅድ፣ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ምክርና የደም ምርመራ፣ የመረጃ፣ የቤተ-መጻሕፍት፣ የኢንተርኔት አገልግሎቶች ወዘተ. ይሰጣሉ::

በወጣቶች ማዕከላት የሚሰጡ አገልግሎቶች ወጣቱን ራሱን ከመጥቀም ባሻገር ቤተሰቡንና የአካባቢውን ሕብረተሰብ ለማገልገልም ዝግጁ እንዲሆን የሚያስችሉ ናቸው:: ይኸውም ልዩ ልዩ ድጋፍና እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸውን ወገኖች (አረጋውያን፣ ኤች.አይ.ቪ በደማቸው ውስጥ የሚገኝ ወገኖች፣ ወላጆቻቸውን ያጡና ተጋላጭ ህፃናት፣ ወዘተ.) በመንከባከብ፣ በአካባቢው በሚደረገው የጤና ልማት በግንባር ቀደምነት በመሳተፍ፣ በተለያዩ የቆዩ ህመሞች ለሚሰቃዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍና ክብካቤ በማድረግ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ:: ይህንንም እውን ለማድረግ የወጣቶች ማዕከላት ለወጣቶች አመቺ ሆነው መደራጀት አለባቸው::

ለዚህም የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ ከሌሎች በወረዳ ደረጃ ከሚገኙ አቻ ሴክተር መ/ቤቶች ማለትም የትምህርት፣ የሴቶች፣ የወጣቶች፣ የውሃ ሃብት፣

ወዘተ. ጋር በመተባበር የወጣት ማዕከላት ተደራጅተው በሚገኙባቸው አካባቢዎች የበለጠ እንዲጠናከሩ የማድረግ፣ በሌለባቸው አካባቢዎች ደግሞ የሚቋቋሙበትን ስልት በመቀየስ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባታል፡፡ በወጣቶች ማዕከል የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ በዋናነት የሚተገበረው በወጣቶች ማዕከል ተመልምለው በሰለጠኑ ግንባር ቀደም የጤና ተባባሪዎች አማካኝነት ሲሆን የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ በዚህ ረገድ የሚጠበቅባት ተግባር ከልዩ ልዩ የወጣት አደረጃጀቶችና ማህበራት በሚኮሉ እወቅና ለሚዋሉትና ለሚሠሩ ለግንባር ቀደም የጤና ተባባሪዎች የአቅም ግንባታና ድጋፋዊ ክትትል ማድረግ ነው፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በወጣት ማዕከላት የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅን በመተግበር ጤናማ ወጣት ለመፍጠር የሚተገበረው የሥራ ሂደት ፍሰት የሚከተለው ገጽታ ይኖረዋል፡ -

- ከወረዳው ውስጥ ካለው የወጣት ማዕከል መረጃ መሰብሰብ
- ከሚመለከታቸው ጋር በመወያየት የጋራ ዕቅድ ማዘጋጀት
- በወጣት ማዕከሉ በግንባር ቀደም የጤና ተባባሪነት የሚያገለግሉትን መመልመልና ማሰልጠን
- ከግንባር ቀደም የጤና ተባባሪዎች ጋር በመሆን እቅዱን ተግባራዊ ማድረግ
- ለግንባር ቀደም የጤና ተባባሪዎች ድጋፍና ክትትል ማድረግ

### 3.2.6.2 በወጣቶች ማዕከል የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅን በተመለከተ የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት አፈፃፀም

#### ሀ/ መረጃ መሰብሰብ፣ መተንተንና ማጠናቀር

የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ ከወረዳው አመራርና ከሕብረተሰቡ ተወካዮች ጋር በመሆን በአገልግሎት መስጫ የወረዳ ክልሏ የሚገኙ የወጣቶች ማዕከላትን በመለየት፣ በማህበር ተደራጅተው የሚገኙ ወጣቶችን በማነጋገር፣ ሰነዶችን በመመርመር፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመወያየት መረጃዎችን ትሰበስባለች፣ትተነትናለች፣ታጠናቅራለች፡፡ መረጃዎቹም በአካባቢው ያለውን የወጣት

ብዛት በዖታና በዕድሜ፣ ወጣቶች ዘንድ ጎልተው የሚታዩ የጤናና የማሕበራዊ ችግሮች፣ በአካባቢው ለወጣቱ ድጋፍ ሊሰጡ የሚችሉ የልማት አጋሮችን፣ የሙያ ማህበራትንና ባለሙያዎችን በመለየት፣ በማነጋገርና በማወያየት መረጃዎችን ታሰባስባለች:: የተቋቋሙ የወጣቶች ማዕከላት የሚያካሂዷቸውን የጤ ፕሮግራሞች በመገምገም ያሉትን ጠንካራና ደካማ ጐኖች ትለያለች::

ለ/ የጋራ ዕቅድ ማዘጋጀት

ከላይ የተሰበሰበውን መረጃ መሠረት በማድረግ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ ከወረዳው አመራር፣ ከልማት አጋሮች፣ከጤና ኮሚቴ፣ከወጣቶች ማህበር፣ ከሴቶች ማህበር፣ ከሴክተር መስሪያ ቤቶች፣ ከሙያ ማህበራት፣ ከታዋቂ ግለሰቦችና ከሃይማኖት አባቶች ጋር ውይይት ታካሂዳለች:: በውይይቱም ወቅት በተደረሰው ስምምነት መሰረት ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮችን በመለየት የጋራ እቅድ ማዘጋጀትና የማስፈጸሚያ ሀብት ማሰባሰብ የሚቻልበት ስልት ከወጣቶች ማህበር ተወካዩች ጋር በመሆን ወረዳው የሚያሰባስብበት ስልት ይነደፋል:: አፈጻጸሙንም ለመከታተል ከላይ ከተዘረዘሩት አካላት የተውጣጣ ቡድን ይሰየማል::

ሐ/ በግንባር ቀደም የጤና ተባባሪነት የሚያገለግሉትን መመልመልና ማሰልጠን

በወጣቶች ማዕከል የግንባር ቀደም የጤና ተባባሪነት ሊያገለግሉ የሚችሉ ወጣቶችን በትምህርት ላይ ካሉና ከትምህርት ውጪ ከሆኑ ወጣቶች መካከል የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ ከሜከሉ ኃላፊዎች፣ ከወረዳው ተወካዮችና ከወጣቶች ማህበራት ተወካዩች ጋር በመሆን ይመለምላሉ:: ምልመላውም ራሳቸውን አርአያ በማድረግ ሌሎችን ለማገልገል ፈቃደኛ የሆኑ፣ በሕብረተሰቡ ዘንድ በመልካም ስነ-ምግባራቸው የታወቁ፣ ሌላውን ለማሳመን የሚችሉና የመግባባት ችሎታ ያላቸው፣ ከተለያዩ ሱሶች ራሳቸውን የጠበቁ፣ ወዘተ ላይ የተመረኮዘ ይሆናል:: እነዚህ ለለውጥ አርአያ የሚሆኑ ወጣቶች ከተመለመሉ በኋላ በወጣት ማዕከል ሊተገበሩ በሚችሉ የጤና ኤክሰቴንሽን ፕሮግራሞችና ንዑስ ፕሮግራሞች ላይ በጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋና በልማት አጋሮች የአምስት ቀን ስልጠና ይሰጣቸዋል:: ስልጠናው ወጣቱ ሕይወቱን ጤናማ በሆነ መልኩ እንዲመራ፣ በራስ መተማመን እንዲኖረው፣ የራሱንና የሕብረተሰቡን ችግር እንዲፈታ፣ በሚያስችል ክህሎት እንዲታነጽ በሚያደርግ መልኩ ተቀርጾ የሚሰጥ ሲሆን አሰጣጡም በተግባር ተኮር ሆኖ በጭውውት (Role play) እና በመስክ ስራ የታገዘ ይሆናል:: በወጣት ማዕከል የሚያገለግሉ ግንባር ቀደም የወጣት የጤና ተባባሪዎች የአምስት ቀን ስልጠናውን

ከወሰዱ በኋላ በቂ ግንዛቤ ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ እንዲቻል የጽሑፍና የቃል ፈተና ይሰጣቸዋል፡፡ የተማሩትንም በቤታቸውና በወጣት ማዕከል መተግበራቸው እንዲሁም የወጣቶችን ችግር ለመፍታት በሚያደርጉት ጥረት ይገመገማል፡፡ በዚህ መሠረት አፈፃፀማቸው አጥጋቢ የሆኑት የወረዳው አመራር፣ ወጣቶችና አጠቃላይ የወረዳው ሕብረተሰብ በሚገኙበት ይመረቃሉ፡፡

መ/ እቅዱን በጊዜ ሠሌዳ መሠረት መተግበር

ወጣት ግንባር ቀደም የጤና ተባባሪዎች ከስልጠና በኋላ በጋራ የተዘጋጀውን እቅድ በተያዘለት የድርጊት መርሀ ግብር መሠረት እንዲከናወን ማድረግ አለባቸው፡፡ የሚከናወኑት ተግባራትም ወጣቱን ከአልባሌ ቦታ ተቆጥቦ ወደ ማዕከሉ በመምጣት በተለያዩ ፕሮግራሞች ላይ እንዲሳተፍ በማድረግ ጤንነቱንና ደህንነቱን መጠበቅ እንዲችል የሚረዱ ተግባራት ናቸው፡፡ ይኸውም በተለያዩ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች፣ በወጣት የስነ-ተዋልዶ ጤና፣ በቤተ መጻሕፍት አገልግሎት፣ በአካባቢው የጤና እና ጤና ነክ ጉዳዮች ላይ የጋራ ውይይት እንዲያደርጉ፣ በተለያዩ የጤና ልማቶች የድርሻቸውን እንዲወጡ፣ በቡድንና በግለሰብ ካውንስሊንግ እንዲሳተፉ ማድረግ ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ወጣቶች የሕብረተሰቡ አካል እንደመሆናቸው መጠን የአካባቢያቸውን ተጨባጭ ሁኔታ በመከታተልና በማጤን እንዲሁም ድጋፍ ሊደረግላቸው የሚገባቸውን የሕብረተሰብ ክፍሎችን በመለየት በዕውቀትና በጉልበታቸው በመጠቀም ለአረጋውያን፣ የቆየ ህመም ላለባቸው፣ ወላጆቻቸውን ላጡ ሕፃናት፣ ለጐዳና ተዳዳሪዎች፣ ወዘተ. አገልግሎት መስጠት አለባቸው፡፡ ለዚህም አገልግሎት ተግባራዊነት ከልማት አጋሮች፣ ከወረዳው ማህበረሰብና አመራር፣ ከብዙኃንና የሙያ ማህበራት ጋር በቅንጅት በመስራት ችግሩ በዘላቂነት የሚቀረፍበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይጠበቅባቸዋል፡፡ የተከናወኑ ተግባራትን በተመለከተ የግንባር ቀደም የጤና ተባባሪዎች በየወቅቱ መረጃዎችን መዝግቦ በመያዝ ለጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ የአፈፃፀም ሪፖርት በወቅቱ ያቀርባሉ፡፡

ሠ/ ለግንባር ቀደም የጤና ተባባሪዎች ድጋፋዊ ክትትል ማድረግ

በወጣቶች ማዕከል የሚከናወኑ ተግባራት የሚጠበቅባቸውን ውጤት እንዲያመጡ ድጋፋዊ ክትትል ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም የጤና ኤክስቴንሽን

ባለሙያ በሁለት ሳምንት አንድ ጊዜ በወጣቶች ማዕከል በመገኘት የእቅድን ክንውን መሠረት ያደረገ ድጋፋዊ ክትትል ታደርጋለች፡፡ በድጋፋዊ ክትትሉም ወቅት የጤና ኤክስቴንሽን ባለሞያዋ ሰነዶች በመመርመር፣ ወጣት የግንባር ቀደም ጤና ተባባሪዎችን ተግባራዊ ስራ ሲያከናውኑ በመመልከትና በማነጋገር፣ የወጣት ማዕከሉን ቅጥር ግቢና አገልግሎት መስጫዎችን በመቃኘት፣ የወጣት ማዕከሉን ተጠቃሚዎች በማነጋገር ይፈጸማል፡፡ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሞያዋ ከግንባር ቀደም የጤና ተባባሪዎች ጋር በጋራ በመሆን በአፈጻጸም ወቅት ባጋጠሙ ችግሮች ላይ ውይይት በማድረግ ችግሮችን ለመቅረፍ የጋራ እቅድ ያቅዳሉ፡፡ ይህም እቅድ በተያዘለት ጊዜ እንዲከናወን ስምምነት ላይ ይደርሳሉ፡፡ በመጨረሻም የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ የድጋፋዊ ክትትልን በተመለከተ ሪፖርት አዘጋጅታ ለቡድን መሪዋና ለሌሎችም አካላት ትልካለች፤ ግብረ መልስም ለወጣት ግንባር ቀደም የጤና ተባባሪዎች ትሰጣለች፡፡

### 3.2.6.3 የጤናማ ወጣቶችና ጤናማ የወጣት ማዕከል መስፈርቶች

በወጣት ማዕከል ጤናማ ወጣቶችና ጤናማ የወጣት ማዕከል ሊባል የሚችለው በማዕከሉ የሚከተሉት ተሟልተው ሲገኙ ነው፡፡

ሀ. ንጹህና በቂ የመፀዳጃ ቤት ለወንድና ለሴት ተለይቶ ሲዘጋጅ፣

ለ. ንጹህና በቂ የመጠጥ ውሃ እንዲሁም የገላ መታጠቢያ /ሻወር/ አቅርቦት ሲኖር፣

ሐ. ወጣቶች ጊዜያቸውን የሚያሳልፉባቸው ለአካልና ለአእምሯቸው መዳበር አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የተለያዩ የስፖርታዊ ፕሮግራሞች ተደራጅተው ሲገኙ፣

መ. የተሟላ የመጀመሪያ ህክምና መስጫ ኪት ሲኖር፣

ሠ. በማዕከሉ የወጣቶች ሰነ-ተዋልዶ ጤና፣ የቤተሰብ እቅድ፣ የኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ የምክር አገልግሎት፣ የአቻ ለአቻ ውይይት፣ አገልግሎቶች ሲኖሩ፣

ረ. በወጣት ማዕከሉ በሕብረተሰቡ የጤና ልማት ላይ በጉልበቱ በዕውቀቱና በቁሳቁስ የነቃ ተሳትፎ ሲያደርግ ነው፡፡

ሰ. የወጣት ሜከሉ ከማኛወም አይነት የቤት ወስጥና የግቢ ቆሻሻ ሁሌም የፀዳና

ወብ ሆኖ ሲገኝ፣

ሸ. ከጤና አካባቢ ፅዳት ጋር የተያያዙ ሚጃዎችን የሚሰጡ ታፔላዎችና ጠቋሚ ሰሌዳዎች አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ላይ ሲገኙ ፣

ቀ. ተጠቃሚ ወጣቶች ለጤና አካባቢ ፅዳት ትኩረት ሰጥተው የሚጋገሩበትና ተግባሪዊ እንቅስቃሴ የሚያደርጉበት ሚደበኛ ኘሮግራም ሲፈጥሩ፣

**ይኸውም ክንውን በጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ ክትትልና ድጋፍ እየተደረገ መስፈርቶቹ መሟላታቸው ሲታወቅ ለጤና ኤክስቴንሽን ሱፐርቫይዘር/ ቡድን መሪ ቀርቦና ግምገማ ተደርጎ የወጣት ማዕከሉ ጤናማ የወጣት ማዕከል ስለመሆኑ ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡**

# ምዕራፍ አራት

# በአዲስ አበባ ከተማ የጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅን ለማስፈጸም የተለያዩ አካላት ያላቸው ተግባርና ኃላፊነት

## 4.1 አጠቃላይ መግለጫ

ለጤና ኤክስቴንሽን ኘሮግራም ተግባራዊነት በየደረጃው አደረጃጀት መፍጠርና የሥራ ኃላፊነት መለየት አስፈላጊ በመሆኑ የከተማና የክ/ከተማ አስተዳድር አካላት ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠትና ተገቢውን የአሠራር ስልት በመቀየስ ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የወረዳው አስተዳድርም በፖኬጁ ላይ ከማቀድ ጀምሮ እስከ መተግበር ድረስ በባለቤትነት የመሳተፍ፣ የመከታተል፣ የመገምገምና የመደገፍ ኃላፊነት አለበት፡፡

"*በአዲስ አበባ ሁሉም መንገዶች ወደ ከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ጸመራሉ*" በሚለ□ መርህ መሰረት ፕሮግራሙን፣ ለመምራት፣ ለማስተባበር፣ ለማስፈፀምና ለመከታተል ከከተማ አስተዳደር እስከ ወረዳ ትረስ የሚኙ የተለያዩ የአስተዳደሩ አካላት በ□□ረጸ□ □ሚቶኑ የሥራ ክፍሎችም ተግባርና ኃላፊነታቸዉን መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 4.2 የከተማ አስተዳደሩ ተግባርና ኃላፊነት

- የጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅን በተሳካ ሁኔታ እንዲተገበር ለሟድረግ አስፈላጊውን የፖለቲካ አመራር መስጠት፡፡
- በከተማዋ የጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ በነዋሪው ህዝባዊ ንቅናቄ እንዲተገበር አስፈላጊውን አመራርና ድጋፍና ክትል ማድረግ፤
- የጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ አፈጻጸም የሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት የሚጠበቅባቸውን ሃላፊነት እንዲወጡና በፖኬጅ ትግበራ ሂደት ቅንጅታዊ አሰራር እንዲያሰፍኑ አስፈላጊውን አመራርና ክትትልና ድጋፍ መስጠት፤
- የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችንና የጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ ሱፐርቫይዘሮችን ለማሰልጠን ለሜቅጠር የሚያስፈልገውን መዋቅርና በጀት መፍቀድ፣

- በየወረዳው አንድ አንድ ጤና ጣቢያዎች እንዲገነቡና አገልግሎት ማስጠት እንዲጀምሩ አስፈላጊውን አመራር መስጠት፡፡ ጤና ጣቢያዎች በየወረዳው እስኪገነቡ ድረስ በጊዜያዊነት የጤና ኤክስቴንሽን ማዕከል ሆነው የሚያገለግሉ ቤቶች በየወረዳው መስተዳድር እንዲዘጋጁ መመሪያ ማስተላለፍ፡፡
- የክ/ከተማ ስራ አስፈጻሚዎች የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅን በባለቤትነት ይዘው እንዲንቀሳቀሱ አስፈላጊውን የሥራ መመሪያና ድጋፍ መስጠት፣
- በከተማው ውስጥ የጤና ኤክሰቴንሽን ፖኬጅ በተቀመጠለት አቅጣጫ እና ለታለመለት ዓላማ መተግበሩና ማረጋገጥ፤ ድጋፋዊ ክትትልና ቁጥጥር እንዲሁም ግምገማ ማካሄድ፣

## 4.3 የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ ተግባርና ኃላፊነት

- የጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅን ግንባር ቀደም አጀንዳ አድርጎ የሚንቀሳቀስ ጠንካራ አደረጃጀትና አመራር መፍጠር፣ በበላይነት መምራት፣
- ለከተማ ጤና ኤክስቴንሽን አገራዊ በሆነው መነሻ መሠረት ሙያተኛ ነርሶችን ለመሟላት በክፍለ ከተሞች የሚደረገውን እንቅስቃሴ ማገዝና ማስተባበር፣
- በማስፈርቱ መሠረት የተማላሙ ሴት ነርሶች የጤና ኤክስቴንሽን ሙያዊና ተግባር ተኮር ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፤
- በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አፈጻጸም ላይ ጥናቶችን ማካሄድ፣ ማስተባበርና መደገፍ፣
- ድጋፋዊ ክትትልና የሥራ ግምገማ ማድረግ፣
- ለክ/ከተማ ጤና ጽ/ቤቶች እና ለወረዳ ጤና ጽ/ቤቶች የቴክኒክና የአስተዳደር ድጋፍ መስጠት፣
- የጤና አጠባበቅ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ማዘጋጀት፣ማምረትና ማሰራጨት፣
- የልምድ መለዋወጫ መድረኮችን ማዘጋጀት፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች እና የበጐ ፈቃድ የሕብረተሰብ ጤና ሠራተኞች አብሮ የሚሠሩበትን ሁኔታ መፍጠርና መደገፍ፣

- ፖኬጅንና በስሩ ያሉ ኘሮግራሞችን **ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ መሠረታዊ የሆኑ ግብአቶች** ገንዘብ፣ ቁሳቁስ፣ የሰው ኃይል ወዘተ..**መኖራቸውን** በየጊዜው **ማረጋገጥና ማሟላት፣**
- **በከተማው ለሚካሄደው የጤና ኤክስቴንሽን** ፖኬጅ ትግበራ **የሚጠቅሙ የመረጃ ሥርዓቶችን ማጠናከርና የሪፖርት ማቅረቢያ ቅጾችን ማዘጋጀት፣**
- **የህሙማን አላለክንና አቀባበልን በተመለከተ** የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ሙያተኛዎችን የሚያበረታታ (empower) የሚያደርግ **መመሪያ ማውጣት፣**
- **ወቅታዊ የሥራ ሪፖርቶችን በማሰባሰብ፣ በማጠናቀርና በማዘጋጀት** ለአስተዳደሩ ከንቲባና **ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ማቅረብ፤** እንደአግባብነቱ **ለሌሎችም አጋር ድርጅቶች ማሳወቅ፣**

## 4.4 የትምህርት ቢሮ ተግባርና ኃላፊነት

ትምህርት ለአንድ አገር አጠቃላይ እድገትና የልማት ግቦች መሳካት ወሳኝ ተግባር እንደመሆኑ መጠን በአተገባበሩ ሂደት ዋነኛ ተዋናይ የሆነውን የትምህርት ቤት ማህብረሰብን ያቀደውን ግብ ከማሳካት ሊያደናቅፈው ከሚችሉት ማንኛውም ጤና ነክ ችግሮች እራሱን መጠበቅና ለሌችም አርአያ የመሆን ጉዳይ አማራጭ የሌለው ተግባር ነው፡፡

በከተማችን የተጀመረውን የጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ የሥራ ቦታ አንዱ ትምህርት ቤቶች በመሆናቸው የትምህርት ቢሮ በከተማችን ፖኬጁን ተግባሪዊ ከማድረግ አንፃር ድርሻው ከፍተኛ መሆኑ ይታመናል፡፡

- የጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጁን በት/ቤቶች ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ጠንካራ አደረጃጀት በመፍጠር ምቹ ሁኔታዎችን መፈጠር፤
- ግንባር ቀደም ተማሪዎችንና መምህራንን ለመምልመል እና ለማደራጀት የሚቻል የአሠራር ሥርዓት/ሥልት መዘርጋት፤
- ፖኬጁን በት/ቤቶች በሞዴልነት ለመተግበር በሚደረገው ተግባር ውስጥ እገዛ መስጠት፤
- በትምህርት ቤቶች የሚገኙ የሥነ ተዋልዶ ጤና እና የፀረ ኤድስ ክበባትን በተጠናከርና ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲንቀሳቀሱ በማድረግ ለፖኬጁ ትግበራ የራሳቸውን ድርሻ እንዲወጡ ማስቻል፤
- በትምህርት ቤቶች ማህበረሰብ አማካኝነት ህብረተሰቡን በማሳተፍ ለፖኬጁ ትግበራ አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ለማድረግ በሚደረገው ተግባራዊ እንቅስቃሴ እገዛ መስጠት፤

- ትምህርት ቤቶች ግቢያቸውን እና አካባቢያቸውን በጽዳትና አረንጓዴነት እንዲይዙ በማድረግ በመማር ማስተማር ምቹ ሁኔታ ከመፍጠር ባሻገር ለአካባቢያቸው እንደ ሞዴል የሚሆኑበት ሁኔታ መፍጠር፤
- የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በትምህርት ቤቶች ወስጥ ገብተው ሥራቸውን የሚያከናወኑበት ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣
- የተሰራውን ሥራ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ በሚወጣው መርሐግብር መሠት ድጋፋዊ የክትትልና ቁጥጥር ሥራ ማሠራት፤

## 4.5 የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ተግባርና ኃላፊነት

- ፖኬጁን በወጣቶች ማዕከላት ወስጥ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል አሠራር በማዘርጋት ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤
- በወጣት ማዕከላት ወስጥ የሚሠሩ የሴክተር ሠራተኞች ከከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ጋር የሚሠሩበትን ሁኔታ መፍጠር፤
- በወጣት ማዕከላት ወስጥ የሥነ ተዋልዶና የኤች አይቪ/ኤድስ አገልግሎትን በአግባቡ ለወጣቱ ለማቅረብ የሚያስችል ሁኔታዎችን መፍጠር፤
- የወጣት አደረጃጀቶችን ለኤክስቴንሽን ፖኬጁ ትግበራ የድርሻቸውን እንዲወጡ ማሥቻል፤
- ወጣቶች በከተማችን ወስጥ በሚደረገው የፖኬጁ ተግበራ የድርሻቸውን መወጣት እንዲችሉና ሞዴል እንዲሆኑ ወደ ንጥናቄ ማስገባት፤
- የተሠራውን ሥራ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ በማሆን ድጋፋዊ ክትትልና ቁጥጥር ሥራ ማሠራት፤

## 4.6 የወጣት ማዕከላት ተግባርና ኃላፊነት

- የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ በወጣት ማዕከላት ወስጥ እንዲተገበር እንዲቻል የማዕከሉ ሠራተኞች እንዲሳተፉ ማድረግ፤
- ወጣቶችን በማደራጀትና ለፕሮግራሙ ሥኬታማነት የራሳቸውን አስተዋጽኦ እንዲወጡ ማስቻል፤
- ፖኬጅን በወጣት ማዕከላት በመተግበር ለአካባቢ ነዋሪ ሞዴል ማድረግ፤
- ወጣቱ የሥነ ተዋልዶና ቤተሰብ ጤና አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ፤
- ወጣቱ የኤች አይቪ የምክርና የምርመራ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ፤
- የተለያዩ የጤና ተግባራትን በሚያመለከቱ ሰርቶ ማሣያዎችን ወጣቶች ተደራጅተው በአካባቢያቸው እንዲሠሩ ማድረግ፤

## 4.7 የኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ ተግባርና ኃላፊነት

- የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ ሥራን ከግንባር ቀደም አጀንዳዎች አንዱ አድርጎ ማንቀሳቀስ፤
- የፖኬጁን ትግበራ በህዝብ ንቅናቄ በማጀብ የህብረተሰብን ንቃተ ጤና ከፍ ማድረግ፤
- የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ከሚተገብሩት ሥልት አንድ የሆነውን የሞዴል ቤተሰብ ምልመላና ሥልጠና በሚዲያ ሽፋን ማጀብ፤
- በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች በመጠቀም የህዝብ ግንኙነት ሥራን አጠናክሮ መቀጠል፤
- በፖኬጁ ትግበራ ወቅት የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችን ለማሥፋት በሚደረገው ሥራ ላይ የሚዲያ ሽፋን ማስጠት፤
- የፖኬጁን ትግበራ በስፖርት መልክ ለህብረተሰብ ማስተዋወቅ፤
- የጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅን ስኬታማ ለማድረግ ባለድርሻ አካላት የድርሻቸውን እንደወጡ ማስቻል፤

## 4.8 የውኃና ፍሳሽ ባለሥልጣን ተግባርና ኃላፊነት

- ባለሥልጣኑ ለነዋሪው የሚያቀርበው ውኃ ከበሽታ አምጪ ህዋሥ ነፃ መሆኑን ማረጋገጥ፤
- የውኃ መሥመር ዝርጋታ ያልደረሰባቸውንና ማስመሩም እያለ በቂና ንፁህ የማጠጥ ውኃ የማይደርስባቸውን አካባቢዎች በመለየት አማራጭና ጊዜያዊ የውኃ አቅረቦት ማዘጋጀት እና ጥራቱን መከታተል፡፡ ለምሣሌ የቦኖ ውኃ፤
- በከተማው የተዘረጉ የውኃ መሥመሮች ብልሽት እንዳይደርስባቸው መከላከል ከደረሰም ፈጥኖ ማጠገን፤
- የሞሉ የግልም ሆነ የህብረተሰብ መፀዳጃ ቤት በፍጥነት ማማጠጥና ማስወገድ፤
- በቂ ቦታ እና አቅም ለሌላቸው አካባቢ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን አማራጭ የጋራ ሽንት ቤት ማዘጋጀት፤
- ከጤና ቢሮ ጋር በመሆን በጋራ በሚወጣው መርሐ ግብር መሠረት ሥራዎችን ማምገምና መረጃ መለዋወጥ፤

## 4.9 የፅዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ተግባርና ኃላፊነት

- የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙዋዎች ቤት ለቤት የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን ሲያስተምሩ ለአፈፃፀሙ እገዛ ማድረግ፤
- ከነዋሪው የእለት ተዕለት ተግባር የሚመነጨውን የደረቅ ቆሻሻ በተቀማጠለት የጊዜ ገደብና አካባቢንና ጤና በማይጎዳ መልኩ ማስወገድ፤
- ከጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ጋር በመሆን ህብረተሰቡን በማስተባበር የህዝብ ንቅናቄ መፍጠር፤
- የከተማው ነዋሪ ስለቆሻሻ  አፀያፊነት ተገንዝቦ ቋሚ የጽዳት ዘመቻ እንዲያካሂድ በጋራ መሥራት፤
- የነዋሪውን ግንዛቤ ለማጨመር በሚደረገው እንቅስቃሴ እገዛ ማድረግ፤
- የፅዳት ሥራ የራሱ የህብረተሰቡ ሥራ እንደሆነ ለማሣመን እና በባለቤትነት ሥሜት ህብረተሰብ እንዲይዘው ለማድረግ በሚደረገው የማህበረሰብ ወይይት እገዛ ማድረግ፤

- በየቦታው ለጊዜያዊ ማከራቀሚያነት የተቀሜጡ የቆሻሻ ገንዳዎችን በወቅቱ ማንሣትና ቆሻሻውን ማስወገድ፣
- በወረዳው አስተዳደር አስተባባሪነት የተሠሩ ሥራዎችን፣ የተገኙ ተሞክሮዎችን እንዲሁም የታዩ ደክመቶችና የመፍትሔ ሃሳቦችን ከከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሞያዎች ጋር በሚገን በጋራ በሚወጣው ሚሔግብር መሠረት መገምገም፣

## 4.10 የክ/ከተማ አስተዳደር ተግባርና ኃላፊነት

- የጤና ኤክስቴንሽን ሠልጣኞችን ምልመላ መከ□ተል፣ ማገገዝና ማስተባበር፣
- በየወረዳው አንድ አንድ ጤና ጣቢያዎችን መገንባት፣
- ለጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ አስፈላጊውን ግብአት (ገንዘብ፣ ቁሳቁስ፣ □ሰ□· □ጅል፣ □□ተ.) ማፈላለግ መመደብና፣
- ድጋፋዊ ክትትልና ቁጥጥር እንዲሁም ግምገማ ማካሄድ፣
- ለወረዳው አስተዳደሮች ስለ ፖኬጁ አፈጻጸም አስፈላጊውን የሥራ መመሪያና ድጋፍ መስጠት፣
- መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በፖኬጁ ዙሪያ አስፈላጊውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ በማስተባበር ቅንጅታዊ አሰራርን ማስፈን፣
- በፖኬጁ አፈፃፀም ዙሪያ የሕዝቡን ተሳትፎና ንቅናቄ ማሳደግ፣
- የጤና ኤክሰቴንሽን ፖኬጅ በታለመለት አቅጣጫ ለታለመለት ዓላማ በክ/ከተማው ውስጥ መፈጸሙን ማረጋገጥ ፣

## 4.11 የክ/ከተማ ጤና ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት

- የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን ግንባር ቀደም አጀንዳ አድርጎ የሚንቀሳቀስ ጠንካራ አደረጃጀትና አሠራር መፍጠር፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ሠልጣኞችን ምልመላ ማገዝና ማስተባበር ፣
- በክፍለ ከተማው በጤና ኤክስቴንሽን አፈጻጸም ላይ ጥናቶችን ማካሄድ፣ ማስተባበርና መደገፍ ፣

- ለወረዳ ጤና ጽ/ቤቶች የቴክኒክና የአስተዳደር ድጋፍ መስጠት ፣
- የጤና አጠባበቅ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ማዘጋጀት፣ ማምረትና ማሰራጨት፣
- የልምድ መለዋወጫ መድረኮችን ማዘጋጀት፣
- በክ/ከተማ ለሚካሄደው የጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ አፈፃፀም የሚጠቅሙ የሪፖርት ማቅረቢያ ቅጾችና የመረጃ አሰባሰብ ሥርዓቶችን ተፅባራዊ ማትረፅ፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ አፈፃፀም የሚዩባቸው የግምገማ መድረኮች ማዘጋጀት፣
- ከአጋር ድርጅቶች ጋር ሊኖር የሚገባውን ቅንጅታዊ አሰራርና ትብብር ማጎልበትና ማጠናከር፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ከበጎ ፈቃድ የሕብረተሰብ ጤና ሠራተኞች ጋር በመመሪያው መሰረት መስራት እንዲችሉ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ፣
- ለክልል ጤና ቢሮ በየወቅቱ ሪፖርት ማዘጋጀትና ማቅረብ፣

## 4.12 የወረዳ አስተዳደር ተግባርና ኃላፊነት

- የጤና ኤክስቴንሽን ሠልጣኞችን ምልመላ መከ□ተል፣ ማገዝና ማስተባበር፣
- በወረዳው ለጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ ተፈፃሚነት አስፈላጊውን ግብአት (ገንዘብ፣ ቁሳቁስ፣ □ሰ□ □ጁል፣ □□ተ.) መመደብና ማፈላለግ፣
- ድጋፋዊ ክትትልና ቁጥጥር እንዲሁም ግምገማ ማካሄድ ፣
- ለወረዳው የጤና ኤክስቴንሽን ባለድርሻዎችና አስፈፃሚ አካላት አስፈላጊውን □ሥራ መመሪያና ድጋፍ መስጠት፣
- መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በፖኬጁ ዙሪያ አስፈላጊውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ በማስተባበር ቅንጅታዊ አሰራርን ማስፈን፣
- በፖኬጁ ዙሪያ የሕዝቡን ተሳትፎና ንቅናቄ ማሳደግ፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ በታለመለት አቅጣጫ እና ለተፈላጊው ዓላማ በወረዳው ውስጥ መፈጸሙን ማረጋገጥ ፣

## 4.13. የወረዳ ጤና ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት

- የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን ቁልፍ ተግባር አድርጎ ማንቀሳቀስ፣
- የከተማ ጤና ኤክስቴሽን ስራዎችን በቤተሰብና በት/ቤት በወጣት ማዕከላት ደረጃ ማስተባበር፣ ተግባራዊ ማድረግ፣ መከታተል፣ መገምገም፣
- ድጋፋዊ የመስክ ክትትልና ግምገማ በማትረፅ ተገቢውን ግብረ መልስ መስጠት ፣
- ለጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች □ሥራ ላይ የሙያ ማሻሻያ ሥልጠናዎች እንዲያገኙ ማስተባበር፣
- ለ□ሮፅራሙ □ሚያስፈልጉ የተለያዩ የጤና አገልግሎት ግብአቶችን፣ ቅጾችን፣ መመሪያዎችን፣ ፎርሞችን፣ ወዘተ. ማሟላት፣
- ከተለያዩ የሥራ ዘርፎችና ከአጋር ድርጅቶች ጋር ቅንጅታዊ አሰራርን ማጠናከር ፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች እንዲቀጠሩ ማድረግና መመደብ፣
- በጤና ኤክስቴንሽን ሰልጣኞች ምልመላ ወቅት ለወረዳዎች ድጋፍ ማድረግ ፣
- ሕብረተሰቡንና አጋር ድርጅቶችን በማስተባበር የጤና ጣቢያ ግንባታን ማስፋፋት፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ከበጎ ፈቃድ የሕብረተሰብ ጤና ሠራተኞች ጋር በመመሪያው መሰረት መስራት እንዲችሉ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ፣
- በወረዳ□ □ስዓ በኤክስቴንሽን ፕሮግራምና ባሉት የጤና ተቋማት የህሙማን አላላክና አቀባበል ሥርዓትን /Referral System / በማጠናከር ለጤና ኤክስቴንሽን ኘሮግራም አፈፃፀም አጋዥና አመቺ ማድረግ ፣
- የሥራ ሪፖርቶችን ማሰባሰብና ማጠናቀር፣ በ□□ቅቱ ለክ/ከተማ ጤና ጽ/ቤት እንዲሁም ለወረዳ□ መስተዳድር ማቅረብ ፣
- አዳዲስ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ሥራ ከመጀመራቸው በፊት የወረዳ□ ጤና ጽ/ቤት ከወረዳ□ አስተዳደር ጋር በመሆን ወደ ተመደቡበት ወረዳ በመውሰድ ከሕብረተሰቡ ጋር የትውውቅ ኘሮግራም ማካሄድ፣
- አዲስ ተመራቂዎች ወደ ሥራ ከመሠማራታቸው በፊት እንደወረዳ□ የጤና ተጨባጭ ሁኔታ ትኩረት የሚሠጣቸውን የጤና ጉዳዮች ጨምሮ ሊኖራቸው የሚገባ የሥራ እንቅስቃሴ፣ የመረጃ አያያዝ፣ የሪፖርት አደራረግና

ከሕብረተሰብና ከበጎ ፈቃድ የጤና ሠራተኞች ጋር እንዴት መሥራት እንደሚገባቸው ሥልጠና መስጠት፣

## 4.14 የወረዳ ጤና ኮሚቴ ተግባር ኃላፊነት

- የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች አካባቢያቸውን ጠንቅቀው እንዲያውቁ እገዛ ማድረግ፤
- ባለሙያዎቹ የሰበሰቡት የጤና መረጃ ላይ በመመርኮዝ የአካባቢውን የጤና ችግር ቅደም ተከተል ከባለሙያዎቹ ጋር ማውጣት፤
- የሞዴል ቤተሰብ አመራረጥና ሥልጠና ላይ እገዛ ማድረግ፤
- በወረዳው ውስጥ የሚገኙትን የበጎ አድራጎት ድርጅትና ባለሃብቶች በማስተባበር የሀብት አሰባሰብ ሥራ ላይ እገዛ ማድረግ፤
- ከጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ጋር በመሆን የወረዳውን /ንዑስ ወረዳውን ዕቅድ አወጣጥ፣ አተገባበር እና የክትትልና ቁጥጥር ሥራ ላይ ጠንካራ ተሳትፎ ማድረግ፤
- የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ሥራን እቅድ ክንውን ማገምገምና የማስተካከያ ሃሣብ ማቅረብ፤

## 4.15. የጤና ጣቢያ ተግባርና ኃላፊነት

- የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በመስክ ልምምድ ተገቢ ሥልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፣
- በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ዕቅድ፣ አፈጻጸም ቴክንካዊ አመራር መስጠትና ትሩኛዊ ክትትል መድረግ፤
- በጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የሥራ ላይ የሙያ ማሻሻያ ሥልጠና ላይ መሳተፍ፣
- □ህሙማን አላላክና አቀባበል ሥርዓትን መሠረት በማድረግ መተግበርና ተገቢውን ግብረመልስ ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች መስጠት ፣
- ለከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ ትግበራ የሚያስፈልግ □ግብአት አቅርቦት ላይ □ድርሻቸውን መወጣት፣
- ከከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ጋር ተገቢውን የመረጃ ልውውጥ ማድረግ ፣

ለከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች □ቅርብ ሙጸዊ ትሩአ ማትረፅ፣

## 4.16 የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ ሱፐርቫይዘር ሥራና □ላፊነት

1. ከስሩ □ሚቶኙትን የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ ባለሙያዎችን □ቅት ሲጸ□ፉ፣ ሲተቶብሩ □ና ሲገመግሙ አብሯቸው ያስተባብራል:: ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል ይገመግማል::

2. ከወረዳ ጤና ጽ/ቤት፣ መስተዳድር፣ ሴክተር መሥሪያ ቤቶች፣ መንግሥ□ዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ሲቪል ማኀበራትና ህብረተሰቡ ጋር በመሆን በወረዳው ችግሮች፣ መፍትሄዎችና አጠቃላይ ጤና ነክ ጉዳዮች ይወያያል በቅንጅት ይሰራል መረጃ ይሰጣል ይቀበላል::

3. □ወረዳ□ ካር□ □ና ኘሮፋይል በማዘጋጀት ሂደት ላይ በግንባር ቀደምትነት ከከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ጋር ያዘጋጃል::

4. □ወረዳው የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች መሠረ□ዊ የመነሻ ጥናት (ቤዝ ላይን ሰርቬይ) በሚሰበሰቡበት፣ መረጃውን በሚያጠናክሩበት፣ በሚተነትኑበትና ችግሮች ለይተው □ቅድ በሚያዘጋጅበት ጊዜ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል ይከ□ተላል::

5. ለኘሮግራሙ ተግባራት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች □ንዲሟሉ በወረዳ□ □ሚቶኘውን ሃብት / □ሰ□ □ይል፣ ፋይናንስና ቁሳቁስ ይለያል:: ለወረዳው መስተዳድርም የሃብት ስርጭት መረጃ በማቅረብ በመስተቴትሩ በኩል ግብዓቶች □ንዲሟሉና አገልግሎት ላይ □ንዲውሉ ያደርጋል::

6. የጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ ባለሙያዎች □ያንዳንዳቸው ከቀፏቸው 500 አባወራዎች 60 ሞዴል ቤተሰብ ግንባር ቀደም ተባባሪ ለማብቃት በመምረጥ ሂደት ላይ ሙያዊ ድጋፍ ጄሰ□ል ጸስተባብራል::

7. ቤተሰቦች የራሳቸውን ችግር በጥረ□ቸው □ንዲፈቱ ለማስቻል በሞዴል ቤተሰብነት በመመልመልና በማሰልጠን ሂደት ላይ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል ይከ□ተላል ጄቶመፅማል::

8. የትምህርት ቤት ሕብረተሰብ በጤና ኤክስቴንሽን ኘሮግራም አማካኝነት ጤናውን ጠብቆ የመማር ማስተማር ሂደት ያለ አንዳች ችግር መከናወን □ንዲችል የግንባር ቀደም ተባባሪዎች ምልመላ ስልጠና □ና ትግበራ ላይ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል ይከ□ተላል ጄቶመፅማል::

9. በወጣት ማዕከላት ላይ በማካሄድ የጤና ኤክስቴንሽን ሥራ የግንባር ቀደም ተባባሪዎች ምልመላ ስልጠናና ትግበራ ላይ ድጋፋዊ ክትትል ያደርጋል::

10. የጤና ትምህርት በርሐ ግብር ከከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ ጋር በመሆን ያቅዳል:: አፈፃፀሙን ያስተባበራል ይገመግማል::

11. የሕብረተሰብ ንቅናቄን ያመቻቻል ያስተባብራል::

12. የጤና ትምህርት አስፈላጊ የሆኑ የጤና መረጃዎችን ያሰባስባል በ□ቅት □ንዲካተት ጸ□ርፉል::

13. የጤና ሴክተር ፖሊሲዎችን □ና □ስትራተጂዎች ይፈፅማል ያስፈፅማል ይከ□ተላል::

14. የሕብረተሰብ ጤና አጠባበቅ ህጎችን ግንዛቤ ጁ□ዓራል::

15. ከከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በግልና በአከባቢ ንጽሕና አጠባበቅ ዙሪያ ለተሻለ ውጤት ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል::

16. □ፅል □ና የአከባቢ ንጽሕና ለመተግበር ለከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችን በ□ቅት □ቅድ አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ድጋፋዊ ክትትል ይሰጣል::

17. በትምህርት ቤት □ና በወጣት ማዕከል ለሚሰጡ የጤና አገልግሎቶች ከከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ጋር ያቅዳል:: □ቅድ አፈፃፀምና ግምገማን ይከ□ተላል ትፉአ ጁሰ□ል::

18. የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የቅድመ ወሊድ ድህረ ወሊድና የቤተሰብ ምጣኔ □ቅድ ጤና ትምህርት □ንዲያስተምሩ አገልግሎት □ንዲሰጡ ሞያዊ ድጋፍ ይሰጣል ጁቶመፅማል::

19. በኅብረተሰቡ □ስዓ □ሚ□ዩት □ናቶችን □ና ህፃናትን የሚጎዱ ጎጂ ልማዳዊ ባህሎች ለመለየትና ለመከላከል የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችን የሞያ ድጋፍ ይሰጣል ይከ□ተላል::

20. ለነፍሰ ጡር □ናቶች ለተወለዱ ጨቅላ ህፃናት የ□ናት ጡት ተጨማሪ ምግቦች ክትባትና □□መሙ ህፃናት ክትትል በሚመለከት ለሚሰጡ ትምህርቶችና አገልግሎቶች ዙሪያ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል ይከ□ተላል ጁቶመፅማል::

21. ኤች አይ ቪ / ኤድስ ከ□ናት ወደ ልጅ □ንዳይተላለፍ በሚሰጡ የትምህርት የምርመራ የሪፈራል አገልግሎት □ቅድ አፈፃፀም ላይ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል ይከ□ተላል ጁቶመፅማል::

22. ለ□ዳጊ ወጣቶች የሚሰጥ የስነ ተዋልዶ ትምህርት ለከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል ይከ□ተላል ጁቶመፅማል: :

23. በቤተሰብ ውስጥ ጤናማ የአመጋገብ ሥርዓት □ንዲኖር ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል ይከ□ተላል ጁቶመፅማል::

24. በኅብረተሰቡ ውስጥ ጤናማ የአኗኗር ዘይቤ ለማስተማርና ለመተግበር ለከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ሙያዊ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል::

25. የኅብረተሰቡ ግንባር ቀደም የጤና ችግር የሆኑ ተላላፊ በሽ□ዎች የኅብረተሰቡ ግንባር ቀደም የሆነ ተላላፊና የማይተላለፍ የጤና ችግሮች ለምሳሌ ኤች አይ ቪ / ኤድስ ቲቢ ወባ የደም ግፊት ስኳር ወዘተ ለመቀነስና ለመቆጣጠር ለከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ሞያዊ ድጋር ይሰጣል ይከ□ተላል ጁቶመፅማል፡፡

26. በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የምክርና የምርመራ አገልግሎት □ንዲሁም በአገልግሎት ሰጪው አነሳሽነት የሚደረግ ምርመራ ለማጎልበት ለከተማ ጤና ኤክቴንሽን ባለሙያዎች ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል ይከ□ተላል ጁቶመፅማል፡፡

27. በከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች አማካኝነት ለሚሰጠው የቤት ለቤት የቆየ በሽ□ ክትትል ድጋፍና ምክር ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል ይከ□ተላል፡፡

28. አስቀድሞ በሽ□ን የመለየት □ንደ ቲቢ በሽ□ ህክምና ያቋረጡትን ተከ□ትሎ □ንዲቀጥሉ የማድረግ ሥራ ላይ የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባሙያዎችን መደገፍ

29. ሕብረተሰቡ ከድንገተኛ አደጋዎች ራሱን □ንዲጠብቅ በማስተማር □ና በአደጋ ጊዜ □መ□መሪጸ □ርቴ□ በመስጠት ሂደት ውስጥ የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ ባለሙያዎችን ሙያዊ ድጋፍ በመስጠት መከ□ተልና መገምገም፡፡

30. በከተማ ጤና ኤክቴንሽን ባለሙያዎች የሚካሄደውን ችግር ፈቺ □ቅድ ዝግጅትና ትግበራ መከ□ተልና መገምገም

31. በስሩ ከሚገኙት የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ሪፖርት መቀበል ማጠናከርና መተንተን ግብረ መልስ መስጠት

32. የክንውን ሪፖርት ለሚመለከ□ቸው አከላት በወቅቱ መስጠት ግብረ መልስ መቀበል

33. ከቅርብ አለቃሉ የሚሰጡት ተጨማሪ ስራዎችን ያከናውናል፡፡

## 4.17 የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ ተግባርና ኃላፊነት

**የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ተጠሪነታቸው በአስተዳደራዊ ጉዳይ ለወረዳው ጤና ጽ/ቤት ሆኖ በቴክኒክ ጉዳይ ለጤና ጣቢያ ወይም ጤና ጣቢያ በሌለበት** ለክ/ከተማ **ጤና ጽ/ቤት ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖራቸዋል፡፡**

4.17.1 **የአስተዳደር ተግባራት**

- በወረዳ □ስዓ □ሚቶች መሰረታዊ የዲሞግራፊና የጤና ነክ መረጃዎችን መሰብሰብና መ□ፅቦ መጸ□፣
- ከወረዳ መስተዳድርና በወረዳው ውስጥ ባሉ ት/ቤቶች ወጣት ማዕከላት ወፀትና ጽዳት አስተባባሪዎች እንዲሁም ከሌሎች አጋር ድርጅቶች ፉር በመተባበር ፕሮግራሙን ማቀድ፣ መምራትና ማስተባበር፣
- ለጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ ተግባራት የሚያስፈልጉ ግብአቶችን ሟሟላትና ማስተዳደር፣
- የህሙማን አላላክና አቀባበል ሥርዓትን ማጠናከርና ተግባራዊ ማድረግ፣
- የመረጃ ማጠናቀሪያ መዝገቦችና ሰነዶች መኖራቸውን ማረጋገጥና መጠቀም ፣
- □□□ሜንቴሽን ሥርዓትን መዘርጋትና የፋይል አያያዝን ማጠናከር ፣
- □ወረዳወን የጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ አተገባበር ክቅት ከሕብረተሰብና ከበጎ ፈቃድ የሕብረተሰብ የጤና ሠራተኞች ጋር በመተባበር ማዘጋጀት፣
- የሚያስፈልጉ መድኃኒቶችንና የሕክምና መገልገያዎችን በወቅቱ መጠየቅ፣ ሲፈቀድም መረከብና በመንግስት የንብረት አያያዝ ገቢና ወጪ በማድረግ በትክክል መጠቀም ፣
- መድኃኒቶችና የሕክምና መገልገያዎች ብልሽት እንዳይደርስባቸው በአግባቡ መያዝ፣ ጊዜ ያለፈባቸውና የማይፈለጉ ሲኖሩ ለክ/ከተማው ጤና ጽ/ቤት ማሳወቅ ፣
- በ□ወቅቱ ሪፖርት በማዘጋጀት ለሱፐርቫይዘሩ፣ለወረዳው ጠፎ ጽ/ቤት፣ ለክ/ከተማ ጤና ጽ/ቤትና እንዲሁም አግባብ ላላቸው አካላት መላ□፣

**4.17.2** ጤናን የማዳበርና በሽታን የመከላከል ተግባራት

- የግንባር ቀደም ጤና ተባባሪዎች ማደራጀት፣ማሰልጠንና ማስተባበር፣
- በመደበኛነት የቤት ለቤት፤በወጣት ማዕከላትና ት/ቤቶች ጉብኝት ማድረግ ፣
- የጤና አገልግሎት ያቋረጡትን መለየትና እንዲቀጥሉ ማድረግ ፣

- በወረዳው ውስጥ ልዩ ልዩ የጤና ማበልፀግና በሽታን የመከላከል /የክትባት አገልግሎት፣ የቤተሰብ እቅድ፣ የጤና አጠባበቅ ትምህርት፣ የሥነ ምግብ ትምህርት፣ የተጨማሪ ምግብ፣ □□መመ ህጻን አመጋገብ፣ የእድገት ክትትል፣የስነምግብ ልየታ፣ የነፍሰጡርና የሚያጠቡ እናቶች አመጋገብ፣ የማይክሮኑትሬት □□ላ፣ የቅድመ ወሊድ የጤና ክብካቤ፣ የማዋለድ አገልግሎት፣ የድህረ ወሊድ  የጤና ክብካቤ፣ የተቀናጀ የህጻናት ህክምና አገልግሎት፣ የጨቅላ ህጻን ክብካቤ፣ የወጣቶች ስነተዋልዶ ጤና አገልግሎት፣ የበሽታዎች አሰሳ ጥናት፣ የግል ንፅህና አጠባበቅ፣የሽንትና የአይነ ምድር አወጋገድ፣ የደረቅና የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ፣ የውኃ አቅርቦትና ንጽሕና አጠባበቅ፣ የምግብ ንጽሕና አጠባበቅ፣ የመኖሪያ ቤት ንጽህና፣ የተባይና የቆር□ሚ እንስሳት ቁጥጥር፣ የቲቢና የወባ በሽታ መከላከልና መቆጣጠር፣ የኤች.አይ.ቪ/ ኤድስና በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች መከላከልና መቆጣጠር/ ተግባራትን ማከናወን፣
- የጤና አገልግሎትን በማስመልከት ሕብረተሰቡን መቀስቀስና በዘመቻ ማንቀሳቀስ፣
- የጤና ፖሊሲና የስትራቴጂ አቅጣጫዎች፣ የጤናውን ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ማወቅና መተግበር ፣

4.17.3 **□መ□መሪጸ □ረጽ** የህክምናና **□ሪ□ራል** አገልግሎትን መስጠት

በማህበረሰብ የጤና አጠባበቅ ሥራ ማከምና መከላከል ተነጣጥለው ወይም ተለያይተው የሚሄዱ አይደሉም:: ህብረተሰቡ በአገልግሎቱ እንዲያምንና በሙሉ ልብ እንዲተባበር ህዝቡ ከሚፈልገውና ከሚያውቀው መነሳት ተገቢ  ነው::

ጻል□፥□፣ አስተማማኝና በቀላል ወጪ በቤታቸው የሚሰጥ ቀላልና አስፈላጊ የህክምና እርቴታና ምክር የመከላከል ሥራ አካል ነው:: በመሆኑም የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ሕብረተሰቡ ለሚፈልገው ምላሽ መስጠት ይጠበቅባቸዋል::

4.16.4 የተለያዩ የመግባቢያ/**□ኮሚኒኬሽን** ዘዴዎችንና **ክህሎትን መጠቀም**

ከላይ የተዘረዘሩትን ተግባራትና ኃላፊነቶች በአግባቡ ለመወጣት የኮሚኒኬሽን ወይም □መግባቢያ ዘዴ ዕውቀትና ክህሎት መታጠቅ አስፈላጊ ነው::

ኮሚኒኬሽን ማለት ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ሰዎች ሐሳብ ተለዋውጠው መግባባት ላይ የሚደርሱበት መድረክ ነው:: ከተግባቡ በሐሳብ አንድ ይሆናሉ ወይም ይተማመናሉ ማለት ነው:: ከተማመኑ ውጤት አለ፤ ውጤት ደግሞ ለውጥ ያመጣል::

በፓኬጁ □ተካተቱ እውነታዎችና ሳይንሳዊ ይዘት ያላቸው ጥልቅ ሐሳቦችን ብቻ ይዞ ወደ ሕብረተሰብ በመግባት ለውጥ ማምጣት ይከብዳል:: ስለሆነም ሐሳቦቹ በኮሚኒኬሽን ክህሎትና ጥበብ ሊ□ቱ□ ጁቁል::

የሚተላለፉ መልዕክቶችም፣

- ፅል□፣ አጭርና ቀላል ለመተግበር ብዙ ጊዜ፣ ጉልበት ወይም ገንዘብ □ማጁ□ጁቁ ፣
- □ቀሜታን የሚያጎሉ፣ ሰዎች ለምን ይህንን ተግባር እንደሚፈፅሙና ምን ዓቅም እንደሚያገኙ የሚያሳውቁ ፣
- □ሚታመኑና ተግባርን በመፈፀም ሊመጣ የሚችለውን ጥቅምና ለውጥ አጉልተው የሚያሳዩ፣
- አዝናኝና ሳቢ ለማድረግ የተለያዩ የመልዕክት ማስተላለፊያ ዘዴዎችን የያዙ ፣
- ለድርጊት የሚገፋፉ፤ ማን ምን ማድረግ እንዳለበት፣ መቼ፣ የትና እንዴት መከናወን እንዳለባቸው የሚገልጹ መሆን ይኖርባቸዋል::

መልዕክቶችን በተለያዩ ዘዴዎች ማለትም ሰው በሰው፣ በትራማ፣ በጭውውት፣ በምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ በሥነ-ቃል፣ በዘፈን፣ በፅዓም፣ ካርድ ሰርቶ በማሳየት፣ □□ተ. ለማህበረሰቡ ማስተላለፍ መለመድ አለባቸው፡፡

## 4.18. የግንባር ቀደም ጤና ተባባሪዎች ተግባርና ኃላፊነት

- አርአያ መሆንና ሌሎች የለውጥ አራማጆችን ማፍራት ፣
- ለጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች አጋዥ በመሆን በጋራ ማቀድ፣ መተግበርና የጤና ሥራዎችን ክትትል ማድረግ ፣
- በትምህርት ቤት እና በወጣት ማዕከላት የጤና አጠባበቅ ትምህርት መስጠት፣
- በጤና አጠባበቅ ዙሪያ ሕብረተሰቡን የትምህርት ቤት እና የወጣት ማዕከላት ማህበረሰብን ማስተባበርና መቀስቀስ ፣
- በአካባቢው ወረርሽኝና አዲስ በሽታ ሲከሰት በፍጥነት ሪፖርት ማድረግ፣

- የጤና አገልግሎት ያቋረጡትን መለየትና እንዲቀጥሉ ማድረግ ፣
- □□ቀዐ ፕሮግራሞች በቤተሰብ በትምህርት ቤት እና በወጣት ማዕከላት መትረሳቸወን መ□ናማቸወን ማረፉቸዓ፣
- በወረዳ የጤና መረጃ አሰባሰብ ላይ መሳተአ፣
- የተከናወኑ ተግባራትን በየጊዜው ለጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኛ ሪፖርት ማድረግ ፣
- የሞዴል ቤተሰቦች ቁጥር እንዲባዙ በሞዴል ቤተሰብ የሚተገበሩ ፓኬጆችን ማስረዳትና ማሳየት፣

## 4.19. □ሞጻል ቤተሰብ ተግባርና ኃላፊነት

- በቤተሰብ አቀፍ የጤና ጠኬጅ እቅድ ዝግጅት፣ አፈጻጸምና ግምገማ ላይ መሳተፍ ፣
- በቁርጠኝነት ስልጠናውን ማጠናቀቅ፣ በስልጠናውም መሰረት መተግበር፣
- በአካባቢው ወረርሽኝና አዲስ በሽታ ሲከሰት በፍጥነት ሪፖርት ማድረግ፣
- በአካባቢው የሚገኙ ቁሳቁሶችን በመጠቀምና የፈጠራ ችሎታን በማከል የቤተሰብ አቀፍ ንዐስ ፕሮግራምን ተፅባራዊ ማትረፅ ፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ስራ ከሞዴልነት አልፎ ወደ ሌሎች አካባቢዎች እየተስፋፋ በቀጣይነት እንዲሄድ ሕብረተሰቡን በአርአያነት ማስተማር፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችና የበጎ ፈቃድ የሕብረተሰብ ጤና ሠራተኞች ሥራ የተሳካ እንዲሆን ተገቢውን ድጋፍ መስጠት ፣

## 4.20. የከተማው ነዋሪ ህብረተሰብ ተግባርና ሃላፊነት

- በወረዳው የጤና ዕቅድ ዝግጅት፣ አፈጻጸምና ግምገማ ላይ መሳተፍ ፣
- የተሰጠውን የጤና አጠባበቅ ትምህርት በተግባር መተርጐም ፣
- በአካባቢው ወረርሽኝና አዲስ በሽታ ሲከሰት በፍጥነት ሪፖርት ማድረግ፣
- በአካባቢው የሚገኙ ቁሳቁሶችን በመጠቀምና የፈጠራ ችሎታን በማከል የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅን ተፅባራዊ ማትረፅ ፣
- በተለያዩ ማሕበራት ተደራጅተው የአካባቢያቸውን የጤና ችግሮች መፍታት፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችና የበጎ ፈቃድ የሕብረተሰብ ጤና ሠራተኞች ሥራ የተሳካ እንዲሆን ተገቢውን ድጋፍ ማድረግ ፣

- በተለያዩ የጤና ንቅናቄ ሥራዎች ላይ መሳተፍ፣
- በመሠረታዊ የጤና አገልግሎት ግንባታና የጤና ክብካቤ ሥራዎች ላይ መሳተፍ፣

## 4.21. ትምህርት ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት

ትምህርት ቤቶች የነቃና ተደራጀ ዜጋን የሚያፈሩ ተቋማት እንደመሆናቸው መጠን ጠ ‚ናን ሊያዳብሩ በሚችሉ ተግባራት ላይ በንቃት መሰማራት ይጠበቅባቸዋል።

የጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅን ከመተግበር አኳያ የመምህራንና የተማሪዎች ሚና በቀላሉ የሚገመት አይደለም። ተማሪው ከእያንዳንዱ ቤተሰብ የወጣ እንደመሆኑ መጠን የጤና መልዕክቶችንና ጭብጥ ተግባራትን ወደ እያንዳንዱ ቤት ለማዳረስ ትልቅ እገዛ አለው። ከዚህም በላይ ጤናማ ትውልድ በመተካት በከተማዋ የጤና ሁኔታ አሁን ካለበት ደረጃ የተሻለ እንዲሆን አስተዋጽኦው ከፍተኛ ነው። ስለሆነም፡ –

- የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ በትምህርት ቤቶች ውስጥ እንደ አንድ ኘሮግራም እንዲተገበር ለማስቻል በፖኬጁ ዙሪያ ሁሉም መምህራን እንዲሳተፉ ማድረግ፣
- ተማሪዎችን ማደራጀትና ስልጠና መስጠት ወይም የትምህርት ቤት የተለያዩ ክለቦች መጠቀም፣
- ፖኬጁን በቤታቸው ለመተግበር ፈቃደኛ የሆኑ ተማሪዎችን በመለየት በመምህራን መሪነት በቡድን ማደራጀት፣
- የጤና ፖኬጁን በትምህርት ቤቶች በሞዴልነት መተግበርና ተማሪዎችን ማስተማር
- ዕድሜያቸው ለአቅመ ሄዋን የደረሱ ሴት ተማሪዎች የክትባት አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ ፣
- የተማሪዎችን የግል ንጽህና መቆጣጠር፣
- የተለያዩ የጤና ተግባራትን የሚያመለክቱ ሰርቶ ማሳያዎችን በት/ቤት በማዘጋጀት የተማሪዎችን እውቀትና ክህሎት ማሳደግ/መጸዳጃ ቤት፣ የእጅ መታጠቢያ፣ የቆሻሻ ጉድጓድ፣ ወዘተ./

- ተማሪዎች በት/ቤት የቀሰሙትን የጤና ትምህርት በየቤተሰቦቻቸው እንዲያስፋፉ ማስቻል፣

መደበኛውን ትምህርት ሂደት በማያስተጓጉል ሁኔታ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በሳምንት የተወሰነ ሰዓት በትምህርት ቤት ስለጤና አጠባበቅ ትምህርት የሚሰጡበትን ሁኔታ ማመቻቸት ፣

## 4.22 የብዙሃን ማህበራት ተግባርና ኃላፊነት

በወረዳ ደረጃ የተደራጁ የሴቶችና የወጣት ማሕበራት በጤና አጠባበቅና በጤና አገልግሎት የመጀመሪያ ተሳታፊም ተጠቃሚ የሆነውን ማሕበረሰብ የሚያቀፉ ናቸው:: በመሆኑም በየማህበራቱ ለጤና ኤክስቴንሽን ኘሮግራም ውጤት አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል:: ስለሆነም፣

- የማሕበራት አመራሮች እራሳቸውን ግንባር ቀደም እና ሞዴል ማድረግ፣
- ሌሎች አባላትን በጤና አጠባበቅ ተግባራት እንዲሳተፉ ማበረታታት፣
- ሴቶችንና ወጣቶችን በጤና ጉዳይ በማሕበረሰብ ውይይት ማሳተፍ፣
- ከጤና ኤክስቴንሽን ሙያተኞች ጋር በመወያየት የአገልግሎት አሰጣጡን እንዲሻሻል ጥረት ማድረግ፣
- በዕቅድ አተገባበርና ግምገማ ላይ መሳተፍ፣
- ከሌሎች የማሕበረሰብ የተለምዶ ማሕበራት ማለትም የዕድር፣ የዕቁብ፣ የሃይማኖት፣ የጽዋ፣ ወዘተ. መሪዎች ጋር በመመካከር ሰፊ የማሕብረሰብ ንቅናቄ ለመፍጠር የበኩላቸውን ድርሻ መወጣት፣

## 4.23. የአጋር ድርጅቶች ተግባርና ኃላፊነት

- ለጤና ኤክስቴንሽን በለሙያዎችና በነሱም በኩል የግንባር ቀደም ጤና ተባባሪዎች የማቴሪያልና የቴክኒክ ትፉአ ማድረግ ፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅን አጀንዳቸው አድርገው መንቀሳቀስ ፣
- በወረዳው ውስጥ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን በመጠቀም የጤና አጠ ባበቅ ትምህርት መስጠት ፣

# ምዕራፍ አምስት

# የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ አፈጻጸም ክትትልና ድጋፍ ሥርዓት

## 5.1 የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ አፈጻጸም ድጋፍና ክትትል

የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ አፈጻጸም ክትትልና ድጋፍ ለማካሄድ ሥራውን የሚመራ አካል መኖሩ አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም በየደረጃው በከተማ፣ በክ/ከተማና በወረዳ የጤና ኤክስቴንሽን ሥራን እንደቁልፍ ተግባር በመውሰድ ድጋፍና ክትትል የሚያደርግ መዋቅር ይዘረጋል፡፡

በመዋቅሩ ያሉ ሙያተኞች ኃላፊነታቸውን በተገቢው መወጣት እንዲችሉ በየደረጃው ያሉት የአስተዳድር አካላትና የጤናው ሴክተር ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ድጋፍና ክትትል ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ሁሉም የሥራ ክፍሎች የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጁ በተፈለገው ሁኔታ መከናወኑን ለማረጋገጥ በተከታታይ ድጋፋዊ ጉብኝት፣ ክትትልና ቁጥጥር በቅንጅት ማካሄድ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በዚህ መሠረት በተለይ በወረዳ ደረጃ ይህ አካል ጠንካራ መሆን ስለሚገባው በወረዳ ጤና ጽ/ቤት የሚመራ ከጤና ጣቢያ ያሉ ሙያተኞችን ያሳተፈ አንድ አካል መቋቋም እንዳለበት ይታመናል። ይህ አካል በወረዳ ደረጃ ድጋፋዊ ክትትልና ቁጥጥር ሲያደረግ የወረዳ አስተዳደር፣ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች፣ ግንባር ቀደም የጤና ተባባሪዎችና ሌሎች የልማት አጋሮች ከሕበረተሰቡ ጋር በመተባበር የሰሯቸውን ሥራዎችና ያጋጠሙ ችግሮችን በጋራ ይገመግማሉ፤ ድጋፍም ይሰጣሉ። በሌሎችም ደረጃዎች የሚደረገው ድጋፋዊ ክትትልና ቁጥጥር ደረጃውን የጠበቀና አስተማሪነት ያለው መሆን ይኖርበታል።

ሕብረተሰቡ የጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅን እንደ ራሱ ጉዳይ አድርጎ እንዲወስድ የሚያስፈልገው ክትትል፣ እገዛና ትምህርት ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል። ከዚህ አንፃር ክትትሉ የተሟላ እንዲሆን ምን ታቀደ? ምንስ ተሰራ? ምንስ ለውጥ ተገኘ? ብሎ ማየት አስፈላጊ ነው።

በመሆኑም መደበኛው የጤናው ሴክተር አጠቃላይ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት እንዳለ ሆኖ መንግስት ለጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ ተግባራዊነት ከሰጠው ልዩ ትኩረት አንጻር በየደረጃው የሚከተሉት የክትትልና ግምገማ ተግባራት መከናወን ይገባቸዋል።

ሀ. በወረዳ ጤና ኰሚቴ ደረጃ

የወረዳ ጤና ኰሚቴ፣ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችንና ግንባር ቀደም የጤና ተባባሪዎችን ባሳተፈ መልኩ በሳምንት አንድ ጊዜ ስብሰባ በማድረግ በፖኬጁ አፈፃፀም ላይ ውይይትና ግምገማ በማካሄድ ሪፖርቱን ለወረዳው ካቢኔ ያቀርባል። ህብረተሰቡም በሕዝባዊ ስብሰባዎች የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አፈጻጸም በመገምገም ጠንካራና ደካማ ጐኖችን በመለየት የሚጠናከርበትንና የሚሻሻልበትን መንገድ ያመቻቻል።

ለ. በወረዳ አስተዳደር ደረጃ

በወረዳ አስተዳደር ተማክሎ እንዲታቀድ ክትትል እንዲደረግና ሪፖርትም በጊዜው እንዲደርስ የወረዳው አስተዳደር የጤና ኤክስቴንሽን እንደ ቁልፍ ስራው ሊወስድ ይገባል። ስለዚህ የወረዳው ካቢኔ በየሁለት ሳምንቱ በመሰብሰብ የወረዳ ጤና ኰሚቴው በአቀረበው ሪፖርት ላይ ውይይትና ግምገማ በማድረግ ተገቢውን ግብረመልስ ለጤና

ኰሚቴው ይሰጣል፡፡ በሌላ በኩል የወረዳው ካቢኔ የቀረበውን ሪፖርትና ግብረመልስ በማጠናቀር ለክ/ከተማው ካቢኔና በግልባጭ ለክ/ከተማው ጤና ጽ/ቤት በየወሩ ያቀርባል፡፡ በተጨማሪም የሕብረተሰቡን ተሳትፎና የብዙኃን ድርጅቶችን /የወጣቶች፣ የሴቶች ማሕበራት/ የሥራ ሁኔታ እንቅስቃሴ በመስክ ሥራ ጉብኝት በማካሄድ በየ15 ቀኑ መገምገምና ግብረመልስ መስጠት ይኖርበታል፡፡

ሐ. በክ/ከተማው ጤና ጽ/ቤት ደረጃ

በክ/ከተማው ጤና ጽ/ቤት የሚመራ ከጤና ጣቢያ ሙያተኞችን ያካተተ ቡድን በማደራጀት በክ/ከተማው ውስጥ ያሉትን ወረዳዎች በመከፋፈል በየወሩ በመስክ በመገኘት ለጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ድጋፋዊ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ያጋጠሙ ችግሮችን ይገመግማሉ፤ ድጋፍም ይሰጣሉ፡፡ በተጨማሪም የክ/ከተማው ጤና ጽ/ቤት ከወረዳ ጤና ጽ/ቤትና ከጤና ጣቢያ የሚደርሰውን ሪፖርትና በመስክ ጉብኝት የተገኘውን ውጤት በማጠናከር በየወሩ በመሰብሰብ ውይይትና ግምገማ በማድረግ ተገቢውን ግብረመልስ ለወረዳው ካቢነ ይሰጣል፡፡ በሌላ በኩል የቀረበውን ሪፖርትና የተሰጠውን ግብረመልስ በማጠናቀር ሪፖርቱን ለከተማው ጤና ቢሮ ያቀርባል፡፡

- በየወሩ በሚደርሰው ሪፖርት መሠረት ግምገማ ያካሄዳል፡፡
- የክ/ከተማ ጤና ጽ/ቤት ጤና ጣቢያዎችንና የወረዳ ጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራሙን ቢያንስ በሦስት ወር አንድ ጊዜ መጐብኘት ይጠበቅበታል፡፡
- ጉብኝቱ በመገምገሚያ መጠይቅ የተደገፈ መሆን ይኖርበታል፣ ከጉብኘቱ በኋላም ግብረ መልስ ይሰጣል፡፡
- በየወሩና በየሩብ ዓመቱ ዕቅድ አፈጻጸምን ይገመግማል፣ ጥሩ አፈጻጸም ያሳዩትን ያበረታታል፡፡ ድክመት የታየባቸውን ችራቸውን በመለየት ድጋፍና የወደፊት የመፍትሄ እቅጣጫ ይሰጣል፡፡
- ሪፖርት አጠናክሮ በየወሩና በየሩብ ዓመቱ ለክ/ከተማው አስተዳደር ያቀርባል፤ ለጤና ቢሮ ይልካል፡፡

መ. በክ/ከተማ አስተዳደር ደረጃ

ከክ/ከተማ ጤና ጽ/ቤትና ከወረዳ አስተዳደሩ የሚደርሰውን ሪፖርት መሰረት በማድረግ፣ በመስክ በመገኘትና ክትትል በማድረግ በየወሩና በየሩብ ዓመቱ ለጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አስፈላጊውን ድጋፍና አመራር መስጠት ይጠበቅበታል።

ሠ. በጤና ቢሮ ደረጃ

በየሶስት ወሩ ለጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ ድጋፋዊ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ላጋጠሙ ችግሮች መፍትሔ ይሰጣል። የከተማው ጤና ቢሮ በየሶስት ወሩ በመሰብሰብ ከፍለ ከተማ ጤና ጽ/ቤት በተላከው ሪፖርት ላይ ውይይትና ግምገማ በማድረግ ተገቢውን ግብረመልስ ለክ/ከተማው ጤና ጽ/ቤት ይሰጣል። በተመሳሳይ የቀረበውን ሪፖርትና የተሰጠውን ግብረመልስ በማጠናቀር ለከተማ አስተዳደሩ ካቢኔና ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሪፖርት ያቀርባል።

## 5.2 የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ አፈጻጸምን በውጤት ለመለካት ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ ጉዳዮች

ሀ. የጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ ሥራን መከታተልና መገምገም ኘሮግሙም በታቀደለት የጊዜ ገደብ፣ ግብና ጥራት መከናወኑን መለካት፣

ለ. የባለሙያ አፈፃፀምን መከታተልና መገምገም የእያንዳንዱን ባለሙያ አስተዋጽኦና ያገኘውን ውጤት ከተቀመጠው ግብ ጋር በማነፃፀር ለመለካትና ተገቢውን የመፍትሔ እርምጃ መውሰድ፣

ሐ. የሀብት አጠቃቀምን መከታተልና መገምገም ከተመዘገበው ውጤት አንፃር በአፈፃፀም የተገኙ ፋይዳዎችን መለካት፣

መ. የተገኘወን ውጤት (Achivement) መከታተልና መገምገም በጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ አማካኝነት ሕብረተሰቡ እንዲያገኝ የታቀደው አገልግሎት ምን ያህል ተግባራዊ እንደሆነና ያስገኘውን ውጤት መለካት፣

ሠ. የሥራ አመራር ተግባራትን ስኬታማነትን ለመለካት የሥራ አመራር ከዋኔ ኦዲት ማድረግ፣

## 5.3 የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ የአፈፃፀም መለኪያዎች እና ጠ ቋሚዎች

### (Performance Measurement Indicators)

| ተ.ቁ | ተግባራት | ጠቋሚዎች |
|---|---|---|
| 1. | የግል ንጽህና | 1.1 የግል ንጽህና ጤና አጠባበቅ ትምህርት የተሰጣቸው ሰዎች ብዛት<br>1.2 የእጅ ጥፍራቸውን ያሳጠሩና ንፅህቸውን የጠበቁ ተማሪዎች ብዛት |
| 2. | ጤናማ የመኖሪያ ቤት | 2.1 ስለጤናማ መኖሪያ ቤት የጤና አጠባበቅ ትምህርት የተሰጣቸው ቤተሰቦች ብዛት<br>2.2 የመኖሪያ ቤታቸውን ለሰውና ለቤት እንስሳት የለዩ ቤተሰቦች ብዛት፣<br>2.3 የግልና የጋራ የገላ መታጠቢያ ያላቸው ቤተሰቦች ብዛት |
| 3. | የምግብ ሐይጅን | 3.1 በምግብ ሐይጅን ላይ የጤና አጠባበቅ ትምህርት የተሰጣቸው ቤተሰቦች ብዛት<br>3.2 በምግብ ወለድ በሽታዎች የተጠቁት ሰዎች ቁጥር መቀነስ |
| 4. | የውኃ ንጽህና | 4.1 በውኃ ንጹህና አጠባበቅ ላይ የጤና አጠባበቅ ትምህርት የተሰጣቸው ሰዎች ብዛት<br>4.2 ለመጠጥ አገልግሎት የሚውልን ውኃ መቅጃና ማጠራቀሚያ የለዩ ቤተሰቦች ብዛት |
| 5. | የመፀዳጃ ቤት አገልግሎት | 2.4 በመፀዳጃ ቤት ላይ የጤና አጠባበቅ ትምህርት የተሰጣቸው ሰዎች ብዛት<br>2.5 መፀዳጃ ቤት ያላቸውና የሚጠቀሙ ቤተሰቦች ብዛት<br>2.6 የቅጥር ግቢያቸውና የመኖሪያ አካባቢያቸው ከሽንትና ሌሎች ቆሻሻዎች ነፃ የሆነ ቤተሰቦች ብዛት፣ |
| 6. | የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ | 2.7 በቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ላይ የጤና አጠባበቅ ትምህርት የተሰጣቸው ሰዎች ብዛት<br>2.8 በየቤቱ የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያና ማስወገጃ ያላቸው ቤተሰቦች ብዛት<br>2.9 የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ያላቸው ቤተሰቦች ብዛት |
| 7. | የቤተሰብ ዕቅድ | 7.1 በቤተሰብ ዕቅድ ላይ የጤና አጠባበቅ ትምህርት የተሰጣቸው ሰዎች ብዛት<br>7.2 ዕድሜያቸው ከ15-49 ዓመት የሆኑ የቤተሰብ ዕቅድ ተጠቃሚ ሴቶች ብዛት<br>7.3 ይኮንዶም ተጠቃሚዎች ብዛት |
| 8. | ክትባት | 8.1 ዕድሜያቸው ከአንድ ዓመት በታች የሆኑና ክትባታቸውን ያጠናቀቁ ሕፃናት ብዛት<br>8.2 ክትባታቸውን ያቋረጡ ሕፃናት ብዛት<br>8.3 የቲቲ ክትባትያጠናቀቁ ሴቶች ብዛት |
| 9. | የእናቶችና ሕፃናት ጤና | 2.10 አራት ጊዜ የቅድመ ወሊድ አገልግሎት ያገኙ ነፍሰ ጡሮች ብዛት<br>9.1 በሰለጠነ የጤና ባለሙያ ወይም በጤና ድርጅት የወሊድ አገልግሎት |

| ተ.ቁ | ተግባራት | ጠቋሚዎች |
|---|---|---|
| | | ያገኙ ሴቶች ብዛት<br>9.2 የጤና አጠባበቅ ትምህርት ያገኙ እናቶች ብዛት<br>9.3 በወሊድ ምክንያት የሞቱ እናቶች ብዛት<br>9.4 የድህረ ወሊድ አገልግሎት ያገኙ እናቶች ብዛት<br>9.5 በአጣዳፊ የመተንፈሻ አካል በሽታ ተይዘው ወደ ጤና ደርጅቶች የተላኩ ሕፃናት ብዛት<br>9.7 በተቅማጥና የሰውነት መሟሸሽ ምክንያት እርዳታ የተሰጣቸው ህጻናት ብዛት<br>9.8 በተቅማጥና የሰውነት መሟሸሽ ምክንያት ለከፍተኛ ዕርዳታ የተላኩ ህጻናት ብዛት |
| 10. | የወጣቶች ስነ-ተዋልዶ | 10.1 የስነ-ተዋልዶ ጤና አገልግሎት ትምህርት የወሰዱ ወጣቶች ብዛት<br>10.2 በሥነ-ተዋልዶ ጤና የምክር አገልግሎት ያገኙ ወጣቶች ቁጥር<br>10.3 ያልተፈለገ እርግዝና ያጋጠማቸው ወጣቶች ብዛት<br>10.4 ያልተፈለገ እርግዝና ገጥሟቸው ወደ ጤና ድርጅት የተላኩ ሴት ወጣቶች ብዛት |
| 11. | ሥነ-ምግብ | 11.1 የስነ-ምግብ ጤና አጠባበቅ ትምህርት የተሰጣቸው ሰዎች ብዛት<br>11.2 ለስድስት ወር የእናት ጡት ማጥባት ብቻ የጠቡ ህፃናት ብዛት<br>2.11 ዕድሚያቸው ከአንድ ዓመት በታች የሆኑና የምግብ እጥረት የታየባቸው ህፃናት ብዛት |
| 12. | ኤች.አይ.ቪ /ኤድስ | 2.12 ስለ ኤች.አይ.ቪ /ኤድስና የአባላዘር በሽታዎች ትምህርት የተሰጣቸው ሰዎች ብዛት<br>2.13 በፍቃደቃነት ላይ የተመሠረተ የምክር አገልግሎትና የደም ምርመራ እንዲያገኙ ወደ ጤና ድርጅት የተላኩ ሰዎች ብዛት<br>2.14 ፀረ ኤች.አይ.ቪ መድኃኒት ለሚወሰዱ ሰዎች የተደረገ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ የተካሄደ ጉብኝት ብዛት |

| ተ.ቁ | ተግባራት | ጠቋሚዎች |
|---|---|---|
| 13. | የቲቢና የሥጋ ደዌ በሽታ | 13.1 ስለ ቲቢና የሥጋ ደዌ በሽታ ትምህርት የወሰዱ ሰዎች ብዛት<br>13.2 የቲቢ ሕክምና የጨረሱ ሕሙማን ብዛት<br>13.3 የቲቢ ሕክምና ያቋረጡ ሕሙማን ብዛት<br>13.4 ከሁለት ሣምንት በላይ ሳል ኖሯቸው ለምርመራ የተላኩ ሕሙማን ብዛት<br>13.5 የስጋ ደዌ ሕክምና በመውሰድ ላይ ያሉ ሕሙማን ብዛት<br>13.6 የስጋ ደዌ ሕክምና ያቋረጡ ሕሙማን ብዛት |

| | | |
|---|---|---|
| 14. | ወባ በሽታ | 14.1 ስለወባ በሽታ መከላከልና መቆጣጠር ትምህርት የወሰዱ ሰዎች ብዛት<br>14.2 ወባን ለመከላከል በአካባቢ ቁጥጥር ላይ የተደረጉ ዘመቻዎች ብዛት |
| 15. | ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች | 15.1 ተላላፊ ስላልሆኑ በሽታዎች ትምህርት የወሰዱ ሰዎች ብዛት<br>15.2 ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ኖሯቸው የምክርና የሕክምና አገልግሎት ያገኙ ሕሙማን ብዛት<br>15.3 የተሰጣቸውን የምክር አገልግሎት ተጠቅመው የባህሪ ለውጥ ያመጡ ሰዎች ብዛት |
| 16. | የአእምሮ ጤና ክብካቤ | 16.1 ስለ አእምሮ ጤና ትምህርት የወሰዱ ሰዎች ብዛት<br>16.2 ለሕክምና ወደ ጤና ድርጅት የተላኩ የአእምሮ ሕሙማን ብዛት<br>16.3 በተለያዩ ሱሶች ተይዘው የምክር አገልግሎት ተሰጥቷቸው የባህሪ ለውጥ ያመጡ ሰዎች ብዛት |
| 17. | ጉዳትና ግጭት መከላከል እና የመጀመሪያ ደረጃ የሕክምና ዕርዳታ | 17.1 ስለ ጉዳትና ግጭት / ጥቃት/ ትምህርት የወሰዱ ሰዎች ብዛት<br>17.2 ጉዳት ደርሶባቸው የመጀመሪያ ደረጃ የሕክምና ዕርዳታ የተሰጣቸው ሰዎች ብዛት<br>17.3 የመጀመሪያ ደረጃ የሕክምና ዕርዳታ ከተሰጣቸው በኋላ ወደጤና ድርጅት የተላኩ ሰዎች ብዛት |

# ምዕራፍ ስድስት

## ልዩ ልዩ ጉዳዮች

### 6.1 ሠነዱን ስለማሻሻል

ይህ ሰነድ ሲዘጋጅ በሀገሪቷ ከተሞች የጤና ኤክስቴንሽንን ለመጀመር በፌደራል ጤና ጥበቃ የወጣውን ረቂቅ የአፈፃፀም መመሪያ ከአዲስ አበባ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር እንዲጣጣም በፍጥነት ወደ ሥራ ለማገባት የተዘጋጀ በመሆኑና የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ በአገራችን የመጀመሪያ ከመሆኑ አንፃር የተገኘ ተሞክሮ ባለመኖሩ የሚቀሉት ነገሮች እደሚኖሩ ታሣቢ በማድረግ በትግበራ ወቅት የሚገኙትን ልምዶች በመቀመር እና ከነባራዊ ሁኔታዎች በማነሣት በቀጣይነት የሚጨሻ ይዘቱን እንደሚይዝ ታሣቢ ተደርጓል፡፡

### 6.2 የባለድርሻ አካላትን ተግባርና ኃላፊነት በተመለከተ

እንደሚታወቀው የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ ትግበራ በአንድ ሴክተር ብቻ የሚከናወን ባለመሆኑ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ተሣትፎ አስፈላጊነት የማያጠያይቅ አይደለም፡ በመሆኑም በሰነዱ ወስጥ የተጠቀሱትም ሆነ በትግበራ ወቅት የሚዛተፉ ባለድርሻ አካላትን ተግባርና ኃላፊነት እንዲሁም ከከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ጋር ያላቸውን የሥራ ግንኙነት አሁን የምንፈራረመውን የመግባቢያ

ሰነድ ማኘ በሚድረግ በቀጣይነት ከነባራዊ ሁኔታ ጋር ተጣጥሞ እንዲሄድ እንደሚደረግ ታሣቢ ተደርጓል፡፡

### 6.3 የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅን ይዘት በተማከተ

የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ ከከተማው ህዝብ አኗኗር፣ አሠፋፈርና የአማገብ ሥርዓት ጋር የተያያዙ ዋና ዋና የጤና ችግሮችን በዘለቄታዊነት ለመከላከልና የህብረተሰቡን ጤና ለማሻልበት ያስችላል ተብሎ በታሰበው በአብዛኛው ከገጠሩ ፖኬጅ የተወሰዱ በአራት የጤና ማሻልበትና የበሽታ መከላከል አበይት ኘሮግራሞች ሥር የሚጠቃለሉ ከ15 ያላነሱ ንዑሣን ኘሮግራሞች ያሉት ሲሆን እነዚህ ኘሮግራሞችና ንዑሣን ኘሮግራሞች ከከተማችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በተግባር ታይቶ ሊሻሻሉ ወይም ባሉበት ሊቀጥሉ እንደሚችሉ ታሣቢ ተደርጓል፡፡

# አባሪ

## አባሪ-1

## የከተማ ኤክስቴንሽን ፕሮግራሙን ለመተግበር በተዋረድ ካለው አመራር ምን ይጠበቃል?

1. ለየወረዳው በተሰጡ ኮታዎችና የምልመላ መስፈርቶች መሰረት ከየወረዳው ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችን መመልመልና ወደ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ መላክ፤

2. በጤና ትምህርቶች ቢያንስ ዲፕሎማ ኖሯቸው ከአራት ዓመት ያላነሰ አገልግሎት በጤና ተቋማትና በጤና ጽ/ቤት ውስጥ ያገለገሉና ፍላጎቱ ያላቸው ጤና ባለሙያዎች በኤክስቴንሽን ሱፐርቫይዘርነት መመደብ ወይም በመጀመሪያ ዲግሪ በጤና ትምህርት የተመረቁ ባለሙያዎችን ለኤክስቴንሽን ሱፐርቫይዘርነት መቅጠር፤

3. ለወረዳው በተሰጡ ኮታ መሰረት የኤክስቴንሽን ባለሙያዎችንና የኤክስቴንሽን ሱፐርቫይዘሮችን ለመቅጠር ወይም ለመመደብ የሚያስችል በጀት ከ2002 በጀት ዓመት በክ/ከተማ ጤና ጽ/ቤት ስር መያዝ፤

4. በዚህ የአፈጻጸም መመሪያ በተጠቀሰው መሰረት በወረዳ ወይም በንዑስ ወረዳ ደረጃ የጤና ኤክስቴንሽን ማዕከልነት የሚያገለግሉ የወረዳ ቤቶች ወይም ትርፍ ጽ/ቤቶችን ማዘጋጀት፤

5. በወረዳው የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን የሚያስተባብር የወረዳ ጤና ኤክስቴንሽን ኮሚቴ ማቋቋም፤

6. በፌደራልና በከተማ ደረጃ የወጣውን አፈጻጸም መመሪያ ከክ/ከተማውና ከወረዳው ነዋሪ ተጨባጭ የጤና ችግር አኳያ በማጣጣም ትግበራ ማንዋል ማዘጋጀት በዚሁም ታግዘው ወደ ትግበራ መግባት፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ፕሮግራሙን ለመተግበር የያዝነውን ይዘን ወደ ትግበራ መግባት፤ ከትግበራ ሂደት መማር፤ ትግበራውን ማሻሻል፤

7. የፕሮግራሙ አፈጻጸም በሁሉም ወረዳዎች በአንድ ጊዜ የሚጀምርበትን ሁኔታ ማዘጋጀት፤ ለፕሮግራሙ አፈጻጸም የተቀመጡ አደረጃጀቶች ሙሉ በሙሉ ተፈጻሚነት እስኪያገኙ ድረስ ከወረዳውና ከክ/ከተማው ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር የሽግግር ጊዜ የአፈጻጸም መርሃ-ግብሮችን ማዘጋጀት፡፡ ለምሳሌ የነባር ክሊኒኮችንና ጤና ኬላዎችን እጣ ፈንታ በዚህ መመሪያ የተመለከተውን መተግበር፡፡

8. በክ/ከተማና በወረዳ ደረጃ ያለው አመራር ፕሮርራሙን ለመምራት የሚያስችለው ግልጽ ዕቅድና ግልጽ የክትትልና የግምገማ መስፈርቶች በማስቀመጥ ወደ አፈጻጸም መግባት፤

9. የፕሮግራሙ አፈጻጸም ከጅምሩ የህዝብ ግንኑነት ስራችን አንድ አካል እንዲሆን ማድረግ፡፡ ለዚህም የሚዲያና ኮሚኒኬሽን ስትራቴጂ መቅረጽና መተግበር፤

10. በየደረጃው በርካታ ህዝባዊ መድረኮችን በመፍጠር ህብረተሰቡ ስለ ፕሮግራሙ ጠቃሚነትና አፈጻጸም ስልቶች ማወያት ከውይይቱ የሚጠቅሙ ግባቶችን መሰብሰብ፡፡ በዚህም ፕሮግራሙን በህዝባዊ ንቅናቄና ተሳትፎ በማጀብ ወደ ትግበራ መግባት፤

11. በክ/ከተማና በወረዳዎች ያሉትን ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመስሪያ ቤት አመራሮችና ሰራተኞችን በማወያየት በፕሮግራሙ አፈጻጸም ዙሪያ የጋራ መግባቢያ ሰነድ እንዲኖራቸው ማድረግና ቅንጅታዊ አሰራርን ማስፈን፤

በአጠቃላይ ተለያዩ ህዝባዊ መድረኮችን በመፍጠርና የፕሮግራሙን አፈጻጸም በሚዲያ ሽፋን በማጀብ በህዝብ ውስጥ ለዘመናት ሰፍኖ የነበረውን ታሞ የመታከም

አመለካከት ከመታመም በፊት በሽታን መከላከልና ጤናን ማጎልበት አመለካከት ቢቻል መተካት ያለበለዚያ የመከላከል አመለካከት የበላይነቱን እንዲይዝ ማድረግ፡፡